“ነገረ-ሙላ”

(የሙላ ነስሩዲን ሆጃ ጣፋጭ ትረካዎች)

በሚኪያስ ጥ.

©መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።

2010 ዓ.ም

ሚኪያስ ጥ.

ማውጫ

“ሙላ ነስሩዲን” 10
1. ሃሰሳ ዘአሮጊት 12
2. ከድጡ ወደማጡ 13
3. ህልም 14
4. ጥያቄዋ 14
5. አማራጭ 15
6. ቅርቃር 15
7. ጭንቀትን ለሌላ 16
8. ብቸኝነት 17
9. ስድቡ 18
10. ማማለል 18
11. የጨለማው ፍሬ 19
12. ቃልና ተግባር 20
13. ፍፁም የለም 20
14. የንግግር ፍራቻ 21
15. ውለታ 21
16. አለማወቅ 22
17. አቅልን መሳት 22
18. ሰካራም ነኝ 23
19. ፍሬ ከናፍር 23
20. ዕጦት 24

21. ተጃጅሎ መጋባት 24
22. አልተግባቡቶም 25
23. ሾፌር አልባ መኪና 25
24. የክብር ደረጃ 26
25. ከድርቆሹ ስር 27
26. ኮተለከሁ 28
27. ወርቃማ ዓሳን ማመስገን 28
28. ጭማሪ እንክብካቤ እሳቤ 29
29. ጥቂት ሃብት 30
30. ደንበኛ ስራ 30
31. አዲስ ነገር 31
32. ዛቻ አጣጣል 31
33. የጥበብ ግርምታ 32
34. ስራ የማግኛ መላ 32
35. ዕብዱን መፈለግ 33
36. የባከነ ዕድል 33
37. ምክርና ገንዘብ 34
38. የብድር ጓደኝነት 34
39. ሁለቱ በረራዎች 35
40. የተያዥ ትዝታ 36
41. ስብከቱ 37
42. ማንን ነው የምታምነው? 38

43. አብርሆት..... 39
44. ቀለበቱ..... 40
45. ተርፈ፟ያለሁ..... 41
46. አፍቅሮት-ዶሮ ጥብስ 41
47. ጉጉቱ 42
48. ፍርጠጣ 42
49. አስክሬኑ..... 43
50. ምርጫ..... 43
51. ምርጫ..... 44
52. አስጠባቂው..... 45
53. ፉክክር አልባ..... 45
54. መደበል..... 46
55. አስታዋሿ..... 47
56. ኢንሹራንስ..... 47
57. የዕይታ ዶክተር 48
58. ባገኝ ኖሮ 48
59. አስተውሎት 49
60. ወይኔ አለመቅመሴ!..... 50
61. እንዳንተ ብሆን 51
62. ግዴታ የለብሽም! 51
63. ዕምነቴን አስወግድ!..... 52
64. ምርጫ..... 53

65. እንቅልፍም እንደአስተያየት 53
66. ከብትና ፈረስ 54
67. ሚስትህ ወ'ት አለች? 54
68. ችሮታ 55
69. ሙያ ቢሱ 55
70. ተሳስቼ ነው! 56
71. አልፎኛል 56
72. ድንኳኑ 57
73. የሰማይ መና 57
74. ምርጫ 58
75. መሳቅ እንደህመም 59
76. መሻሻጥ 60
77. ሰይጣኑ ጋር 61
78. አያ'ዎ! 62
79. ስሁቱ ጥያቄ 62
80. ልዋጭ 63
81. ፀላኤ ጭቅጭቅ 64
82. የሚስት ዳፋ 65
83. ለመርሳት መጣር 65
84. ፀገም 66
85. አላዋቂነት 67
86. ወረፋው 67

87. ተመሳስሎሽ 68
88. ንዴት 69
89. ያልተፈወሰ በሽታ 70
90. ሴት? ወንድ? 70
91. የመጨረሻ መለኪያ 71
92. መታከት 71
93. ጠንካራው ውሻ 72
94. የሴት ግብር 73
95. መጠጡ 73
96. ታቃጥላለች... 74
97. ፍንክንክ 74
98. ሁለቱን ለምን? 75
99. ፍሬ ከናፍር 75
100. ማብሸቅ በሙዚቃ 76
101. ንብረቶቼን 76
102. ልጅነትን መፈለግ 77
103. ብዝኀ-ስህተት 77
104. ትመጣለህ! ትመጣለህ! 78
105. «ማረጀት ፀረ-ሞት ነው!» 78
106. ህመም 79
107. «ሰብዓዊ መብት ይከበር!» 79
108. በአባቱ የወጣ ልጅ 80

109. የተዝናኖት ጉዞ 81
110. ምኞት 81
111. ምክሩ 82
112. ተፈላጊው በቅሎ 82
113. ተነቃዩ ጥርስ 83
114. ስሞታ 83
115. ውርስ 84
116. ኬረዳሽ 85
117. ዕውነታ 86
118. ችጋርን መቃረም 87
119. ሃሳዊ ዜና 87
120. አማች 88
121. ተከታይ ተፈንካች 89
122. ጢምቢራን ማጣት 90
123. ዕድል 90
124. መረፃ ደቂአንስቲዮ 91
125. ሰርቆ መመለስ 92
126. ስሜትን መግፋት 92
127. ክህደትን ፍለጋ 93
128. ብድርን መግፋት 93
129. ጨረታው 94
130. ማስጠሎ ፅሁፍ 95

131. ዕውነተኛ አመንዝራ..... 96
132. ችጋርን መሻት..... 97
133. ችግርን መጠበቅ..... 98
134. ግብጥው..... 99
135. ኮንሰርቱ..... 99
136. ተምሳሌተ-ጉንዳን..... 100

“ሙላ ነስሩዲን”

ሙላ ነስሩዲን አፊያሹር ሰው ነው፤ ሱፊስትም ነው። በአሁኗ ቱርክ፥ ሲቪሪሳር በምትባል ከተማ ተወለደ። በ13ኛው ክፍለ-ዘመን ውስጥ በኤክሺር ከተማ አረፈ። በሞተባት ከተማ ትልቅ ሃውልት ቆሞለታል። በየዓመቱ ዓለምዓቀፍ የነስሩዲን ሆጃ (ሙላ ነስሩዲን) ፌስቲቫል እ.ኤ.አ ከነሃሴ5-10 ድረስ የሞተባት ከተማ ውስጥ ይከበራል።

ፕ/ር ሚካኤሊ ባይራም በሰፊው እንደሰሩት ጥናት ከሆነ፥ የሰውዬው ሙሉ ስም ናስርዐዲን ማህሙድ አልኮይ ነው፤ ከመጠሪያ ስሙ በፊት “እሂ ኤቭራን” የሚል የማዕረግ ስም ተሰጥቶታል-የተወለደበትን ጎሳ ለማሳየት። ጥናቱ እንደሚያሳየው ኮይ በተባለች፥ ኢራን ውስጥ በምትገኝ ምዕራባዊ አዘርባጃን ግዛት ውስጥ ተወለደ። ትምህርቱን ኮሆረሳን ከተማ ተማረ፤ የታዋቂው የቁራን ሙፈዚር ፈቃሃር አልዲን አልራዚ ደቀ-መዝሙር ሆኖ፥ ሄራት ከተማ ተምሯል።

በጊዜው በነበረው ንጉስ(ካሊፍ) ወደአናቶሊያ ተላከ፤ በጊዜው የሞንጎሊያውያንን ወረራ ለመቋቋም።

ካይሴሪ ከተማ ውስጥ እንደ”ካዲ”(ኢስላማዊ ዳኛና እንባ ጠባቂ) ሆኖ ሰርቷል። በቀልዶቹ ውስጥ የሚሰገስጋቸው የኢስላማዊ የህግ ሃሳቦች ከሃይማኖት ብቻ ሳይሆን ከዚህ ስራው የመጡ መሆናቸውን እንረዳለን። የፐርሺያው ሩሚ ቀንደኛ ተቀናቃኝ ነበር። ሙላ ነስሩዲን በርካታ ከተማዎች ውስጥ ኖሯል። የእርሱ ታሪኮች ከቱርክ እስከአረብ ባህል ውስጥ እንደሁኔታው ተዛምደው ይታያሉ። ከፐርሺያ እስከአፍጋኒስታን፥ ከሩሲያ አስከቻይና ቀልዶቹ ይወራሉ። በየጊዜው በ”ነስሩዲን” ስም አዳዲስ ቀልዶች ይፈበረካሉ፤ ይወራሉ። የተረቶቹ መቼቶች በአብዛኛው ትንንሽ መንደሮች ናቸው። አብዛኛዎቹ ቀልዶቹ በወረቀት ላይ የሰፈሩት በ1571 አካባቢ እንደሆኑ፥ የታሪክ መዛግብት ይጠቁማሉ። የነስሩዲን ቀልዶች በዓረቡ ዓለም በሰፊው ይተረካሉ። እኛም በትንሹ ተርጉመን፥ በአማርኛ አፍ “ቀልድ” ተብዬዎችን አቅርበናል።

• ሃሰሳ ዘአሮጊት

አንድ ሃብታም ገበሬ ልጆቹን ለመዳር እየሞከረ ነው፤ ውስጡ ግን በተስፋ መቁረጥ ስሜት ተሞልቷል። በዚሁ ስሜት እየታመመ በነበረበት ጊዜ፥ ሙላ ነስሩዲን ጋር ይገናኛል።

“ብዙ ልጆች አሉኝ።” ነገሩን ለሙላ ሲያስረዳ፥ ”ሁሉም ተመችቷቸው እንዲኖሩ የልብ ፍላጎቴ ነው። እናም፥ የባሎቻቸው ጥገኛ እንዳይሆኑ በባንክ ውስጥ ብዙ ገንዘብ አስቀምጥላቸዋለሁ። ትንሿ ልጄ ዕድሜዋ 23 ነው፤ በምታገባበት ጊዜ 25,000 ሩፒ በባንክ አካውንቷ አስገባለሁ። ሁለተኛዋ ልጄ ደግሞ፥ ዕድሜዋ 32 ነው፤ እርሷም በምታገባበት ወቅት፥ 50,000 ሩፒ በራሷ አካውንት አስገባለሁ። ሶስተኛዋ ልጄ ዕድሜዋ 43 ሲሆን፥ በምትዳርበት ወቅት 75,000 ሩፒ በልጅቷ ስም በተከፈተው አካውንት አስቀምጣለሁ። ”

“በጣም ደስ ይላል!” አለ፤ ነስሩዲን፥ ”ዕድሜዋ ሃምሳ የሆነች ልጅ ብትኖርህ ኖሮ፥ በጣሙን ይደንቀኝ ነበር። ”

⁘⁘⁘

• ከድጡ ወደማጡ

የሙላ ነስሩዲን ቤተሰቦች እጅግ ተናድደዋል፤ እርሱ ለማግባት የሻታት ልጅ ኢ-አማኒ ናትና።

“ኢ-አማኒ ማግባት የለብህም።” የሙላ እናት በአንክሮ ተናገሩ።

“ታዲያ! ምን ማድረግ እችላለሁ? በጣም’ኮ ነው የምወድዳት!” ወጣቱ ነስሩዲን።

“ጥሩ!” እናቱ፤ በተለሳለሰ አንደበት፥ ”ልጂቱ የምትወድህ ከሆነች፥ አንተ ‹አድርጊ› ያልካትን ነገር በሙሉ ልቧ ታደርጋለች። በጽናት ከተጋህ አስተሳሰቧን መለወጥ ትችላለህ። ”

ህልቄ-መሳፍርት ሳምንታት ከነጎዱ በኋላ፥ አንድ ጠዋት ላይ ነስሩዲን ከመላ ቤተሰቡ ጋር ቁርስ ሊበላ ተሰየመ። የልብ ስብራቱ በፊቱ ላይ በግልጽ ይነበብ ነበር።

“ምነው? ችግር አለ?” ሲሉ፤ እናትዬው ጠየቁ፥ ”ከወዳጅህ ጋር ጥሩ አካሄድ ነበረህ፤ ደግሞም በሃይማኖት ጉዳይ ላይ ተለሳልሳለች። ”

“እርሱ’ኮ ነው ችግሩ!” ነስሩዲን መለሰ። ”ሁሉንም ነገር በትክክል ፈጽሜያለሁ። ትናንት ማታ ግን በሃይማኖትና በጌታ መኖር አምና ለመመንኮስ እንደወሰነች ነገረችኝ። ”

⁘⁘⁘⁘⁘

• ህልም

ቆንጆይቱ ልጅ በጥልቁ ተስፋ አድርጋ ነበር-ከነስሩዲን ጋር ለመጋባት። ሙላ ነስሩዲን ግን የጋብቻ ጥያቄ አንድም ቀን ጠይቋት አያውቅም። አንድ ምሽት ሙላ ለልጅቷ እንዲህ አላት፥

“ትናንት ማታ ያልተለመደ ህልም አለምኩ፤ አንቺን ለጋብቻ ስጠይቅ። የህልሜን ፍቺ ባውቅ ምንኛ ጥሩ ነበር።” ሲል፤ ቆንጆይቱ ካ’ፉ ለቀም አደረገችና፥ ”የህልምህ ፍቺ ምን መሰለህ? የአሳቢነትህ ዛር የሚቀሰቀሰው ስትተኛ እንጂ ስትነቃ አይደለም፤ ፍቺው ይኸው ነው። ”

⁘⁘⁘

• ጥያቄዋ

“እኔን በጣም አታፈቅረኝም!” የሙላ ነስሩዲን ሚስት ተናገረች፤ እንባዋን እያዘራች። “እንደዚህ እያነባሁ ‹ምን ሆንሽ? › ብለኸ አልጠየቅኸኝም። ”

“ይቅርታ፥ ውዴ!” አለ፤ ነስሩዲን፥ ”ግን ይህ አይነቱ ጥያቄ ብዙ ገንዘብ እያስወጣኝ ነው። ”

⁘⁘⁘

• አማራጭ

ሙላ ነስሩዲን የከንፈር ወዳጁ ጋር ለዓመት ያህል ይገናኝ ነበር፤ ቤቷ ድረስ እየሄደ። አንድ ምሽት ነስሩዲን ከቤቷ ሲወጣ፥ የርሷ አባት አስቆመውና ጠየቀው፥ ”አንተ ልጅ! ለአንድ ዓመት ያህል ደጇን እየጠናህ ከልጇ ጋር ስትገናኝ ነበር፤ ሁሌም አይሃለሁ። ግን አንድ ማወቅ የምፈልገው ነገር አለ። ለ’ሷ ያለህ ሃሳብ ወይም የወደፊት አላማህ የተከበረ ነውን? ወይስ አይደለም? ”

የነስሩዲን ፊት ባ’ንዴው ተቀያየረ፥ ”ምን ማለት ፈልገህ ነው፥ ጌታው? ከ’ሷ ሌላ አማራጭ ‹አለህ› እያልከኝ ነው? ”

⁘⁘⁘

• ቅርቃር

“ደግ! ...የልጇ ባል መሆን እንደምትፈልግ በጥሩ ሁኔታ ተረድቼያለሁ።” አባትዬው ለልጃቸው እጮኛ ተናገሩ።

ሙላ ነስሩዲን፥ ”ጌታዬ! እርግጠኛ አይደለሁም። ግን ልጅዎትን ባገባ፥ እንዴት አድርጌ ፍቺውን እንደምፈጽም አንድዬ ብቻ ነው የሚያውቀው።” አላቸው።

⁘⁘⁘

• ጭንቀትን ለሌላ

የሙላ ነስሩዲን እናት ለልጇ ደህንነት ሁሌ ትጨነቃለች-ሌሎች እናቶች ለልጆቻቸው እንደሚጨነቁት ሁሉ።

አንድ ቀን ሙላን፥ ”ሁልጊዜ ወደክፍልህ ‹ሴት ይዘህ አትግባ› ብዬ አላስጠነቀቅኩህ’ም? ለምን ትናንት ማታ ሴት ይዘህ መጣህ? እንደዚህ ያለ ነገር እንዴት እንደሚያስጨንቀኝ መቸም ታውቃለህ።” ስትል ጠየቀችው።

“ግን እኔ’ኮ ‹ሆነ› ብዬ ወደምኝታ ቤቴ አላስገባኋትም።” አለ፤ ነስሩዲን፥” እኔ ነኝ-ወደ’ርሷ ክፍል የሄድኩት። እንግዲህ የራስሽን ጭንቀት ሙሉበሙሉ ለፍቅረኛዬ እናት ማስረከብ ትችያለሽ።”

፡፡፡፡፡

- **ብቸኝነት**

ሙላ ነስሩዲንና ጓደኛው ተቀምጠው እየተጨዋወቱ ነው፤ ሙላ በቅርቡ ስለመከነው የፍቅር ግንኙነቱ እየተረከ ነው።

“ማለት...” ሲል፥ ጠየቀ፤ ጓደኛው፥ ”ለ’ርሷ ስትል ነው-መጠጣት፥ ማጨስ፥ ቁማርና ከረንቡላ መጫወትና መጨፈር የተውከው? ”

“አዎ፥ ምክንያቱም እርሷ በጣም ችክ አለችብኝ።” አለ፥ ሙላ።

“ከዛ በኋላ ለምን አላገባህትም?” ደግሞ ጠየቀ፤ ጓደኛው።

“ሁሉንም ነገር ካስተካከልኩ በኋላ...” አለ፤ ነስሩዲን፥ ”በጥሩ ሁኔታ ለመኖር ስለወሰንኩ ነው ያላገባኋት። ”

⁞⁞⁞

• ስድቡ

አንድ የራት ግብዣ ላይ የከንፈር ወዳጁ ሙላ ነስሩዲንን እንዲህ አለችው፥

“ሁልጊዜ ‹ደደብ› የሚል ቃል ከአንደበትህ ስታወጣ እሰማለሁ። በ’ርግጠኝነት፥ በዚህ የቃል ምድብ ውስጥ እኔን እንዳልቀረጥከኝ አምናለሁ። ”

“ፍቅሬ! በጣም ትዕቢተኛ አትሁኚ-በዓለም ላይ ደደብ ባይኖርም እንኳ!” አላት፤ ሙላ።

፨፨፨፨

• ማማለል

ሙላ ነስሩዲን ወንበር ላይ ተቀምጦ፥ ከባልዲ ሙሉ ውሃ አሳ ያጠምዳል። አንድ ጎብኚ ሙላ በተቀመጠበት በኩል በሚያልፍበት ጊዜ፥ አሳ ሲያጠምድ ይመለከተዋል። በጓደኝነት ስሜት ተነሳስቶ፥ ”ምን ያህል አሳዎችን አጠመድክ?” ሲል፤ ጠየቀው። ሙላም፥ ”ስምንት አጥምጄያለሁ፤ ዘጠነኛው ተጠማጅ ደግሞ አንተ ነህ!” ብሎ፥ መለሰለት።

፨፨፨፨

• የጨለማው ፍሬ

አንድ ምሽት ላይ የሙላ ነስሩዲን አባት ከምኝታ ቤታቸው አጠገብ ወደሚገኘው በረት፥ ፋኖስ አብርተው ገቡ። በረቱ ውስጥ ያለውን ሁኔታ “ለማየት” ብለው የገቡት አባት፥ ሳያስቡት ከልጃቸው ጋር ይገጣጠማሉ። ሙላም ፋኖስ ይዟል።

“እንደዚህ ሽክ ብለህና ፋኖስ ይዘህ፥ በረት ውስጥ ምን ትሰራለህ?” ሲሉ፤ አባት ጠየቁ።

“ፍቅረኛዬን እዚሁ ላመጣት ነው፥ አባዬ።” አለ፤ ነስሩዲን፥ ”በድርድር እንጨቶች መካከል መሄድ አለብኝ። ግን ጨለማ ነው። ”

“ልክ በአንተ ዕድሜ በነበርኩበት ጊዜ፥ እናትህን ለመጥራት ለመጀመሪያ ጊዜ ስሄድ፥ በድርድር እንጨቶቹ መካከል ሳልፍ ፋኖስ አልያዝኩም ነበር።” አሉ፤ አባትዬው።

“አውቃለሁ!” ነስሩዲን መለሰ፥ ”ግን እንደዛ ለፍተህ ምን እንዳገኘህ አስተውለህ ተመልከት፥ አባዬ! ”

⁘⁘⁘⁘

• ቃልና ተግባር

“ውዴ! ላንተ ስል፥ ለመሞት ዝግጁ ነኝ!” አለች፤ የምታምረዋ ሴት።

“ሁልጊዜ እንደዚህ እያልሽ ቃል ትገቢያለሽ። አንድም ቀን ግን ተግብረሽው አታውቂም!” አላት፤ ሙላ።

፡፡፡፡፡

• ፍፁም የለም

ወጣቲቱ በፍቅረኛዋ-በሙላ ነስሩዲን በጣም ተናድዳለች፤ ”አንተ የለየልህ ሰካራም ነህ!” አለችው።

“ተዪ! ራስሽን አትሸንግዪ!” አላት፤ ነስሩዲን፥ ”ሁላችንም’ኮ ፍጹማን አይደለንም። ”

፡፡፡፡፡

• የንግግር ፍራቻ

ሙላ ነስሩዲን ህዝብ ፊት ቆሞ የመናገር ድፍረት የለውም፤ አንድ ቀን-ታዲያ-የራት ግብዣ ማሳረጊያ ላይ እንዲናገር ተጋበዘ። ወደመድረኩ እየተንቀጠቀጠ ወጣና ምንተባተብ ጀመረ።

“የ...የኔ ጓደኞች! እዚህ ቦታ ተጋብዤ ስመጣ፥ ምን አይነት ንግግር ለእናንተ እንደማቀርብ ከጌታ ጋር እየተመካከርኩ ነበር። ግን ለጊዜው እኔ አይደለሁም-ንግግሬን የማውቀው፤ ጌታ ነው የሚያውቀው! ”

⁘⁘⁘

• ውለታ

ጋብቻቸውን እንደፈጸሙ፥ የመጀመሪያ ራታቸውን በጋራ ተመገቡ፤ ሚስትዬው ባሏን-ሙላ ነስሩዲንን እንዲህ ስትል ጠየቀችው፥

“የኔ ውድ! ሁሌ እንደዚህ የጣፈጠ ራት በየቀኑ ብሰራልህ፥ ምን ትሰጠኛለህ? ”

“የኔን የህይወት መድህን!” አለ፤ ነስሩዲን።

⁘⁘⁘

• አለማወቅ

ወጣቷ የሙላ ነስሩዲን ባለቤት ገና ከጫጉላ ቤት ከመውጣቷ፥ ባሏን ማብጠልጠል ጀመረች፤ ከጓደኛዋ ጋር በተገናኘች ቁጥር፥ ስለባሏ የመጠጥ ሱስ እንደለፈለፈች ነው።

“ሰካራም መሆኑን እያወቅሽ፥ ለምን አገባሽው?” ስትል፥ ጓደኛዋ በግርምት ጠየቀቻት።

“በጣም እንደሚጠጣ ባለፈው ምሽት ሰክሮ እስከሚመጣ ድረስ አላውቅም ነበር። ” የነስሩዲን ባለቤት መለሰች።

፨፨፨

• አቅልን መሳት

ሙላ ነስሩዲን ከፈተና ጣቢያ ወደቤቱ ለመመለስ፥ መንገዱን ተያይዞታል፤ የመጀመሪያ እርዳታ አሰጣጥ ፈተና ተፈትኖ ስላለፈ፥ የምስክር ወረቀት ተሰጥቶታል። በሚጓዝበት ጊዜ፥ አንድ ሰው በአፍጢሙ ተደፍቶ ይመለከታል። ሙላ በድንጋጤ ወደሰውዬው ዘንድ ሄዶ፥ ሰውዬው አፍ ላይ አፉን ገጥሞ ትንፋሽ ይሰጠው ጀመር። ከደቂቃዎች በኋላ፥ ሰውዬው ተነሳና ተናገረ፥

“ጌታው! ምን እየሰራህ እንደሆነ ላውቅ አልቻልኩም። እኔ ግን ወደዚህ የቆሻሻ ጉድጓድ እንደአሣ ተወርውሬ ለመግባት ነበር ሃሳቤ። ”

፨፨፨

• ሰካራም ነኝ

ሙላ ነስሩዲን በሃይለኛው ጠጥቶ ሰክሯል። በዙሪያው የሚገኙት ሰዎች፥ የእግር ኳስ ጨዋታ እየተመለከቱ ነው። የሙላ ማላዘን ከፉኛ ስላስቸገራቸው ለሙላ አርፎ የማይቀመጥና ዝም የማይል ከሆነ፥ ፖሊስ እንደሚጠሩ በዛቻ ዘይቤ ይነግሩታል። እርሱም፥ ”የታለ ፖሊሱ! አሳዩኝ! ሰካራም እንደሆንኩ እነግረዋለሁ!” ሲል፤ መለሰላቸው።

ቃላቶቹን በተናገረበት ቅጽበት፥ አንድ ቁመቱ ስድስት ጫማ የሆነ ፖሊስ ከፊቱ ተደንቅሮ፥ ”እኔ ፖሊስ ነኝ!” አለው።

“አው! ደስ ይላል!” አለ፤ ነስሩዲን፥ ”እኔ ሰካራም ነኝ! ”

⁞⁞⁞⁞

• ፍሬ ከናፍር

ሙላ ነስሩዲን ሁል’ዜ እንዲህ ይል ነበር፥

“እያንዳንዱ ወንድ ቢያንስ አንድ ሚስት ማግባት አለበት፤ ምክንያቱም መንግስትን ላለመውቀስ ጥቂት ሰበቦችን አናጣምና። ”

⁞⁞⁞⁞

• ዕጦት

ምርኩዙን ይዛ በመደገፍ ሙላ ነስሩዲንን ያገዘቸው ሴት፥ እርሱን ለማዋራት በጣም ጓጉታ እንዲህ አለችው፥

“ሽባ እንደመሆን የሚሰቀጥጥ ነገር የለም። ግን አስታውስ፥ ምን ያህል ዓይነ-ስውር ከመሆን እንደሚሻል! ”

“ልክ ነሽ! እህቴ!” አላት፤ ሙላ፥ ”አይነስውር ብሆን ኖሮ፥ ሰው ሁሉ ሳንቲሙን እየወረወረልኝ ይሄድ ነበር! ”

⁘⁘⁘

• ተጃጅሎ መጋባት

ሙላ ነስሩዲንና ባለቤቱ እየተጨቃጨቁ ነው።

“ያኔ አንተን ሳገባ ጅል ነበርኩ።” ተናገረች፥ ሚስት።

“ስገምት፥ ዕውነትም ጅል ነበርሽ።” አለ፤ ነስሩዲን፥ ”ግን እኔም-ራሱ-ጅል ነበርኩ፤ ከቁምነገር አልጻፍኩትም እንጂ! ”

⁘⁘⁘

• አልተግባብቶም

አንድ ወጣት አባት ልጁን ለማባበል እየጣረ ነው፤ ማባበሉን የሚፈጽመው በርጋታና በድፍረት ነው። ቦታው መንገድ ዳር ስለሆነ፥ ህጻኑን ለማረጋጋት ብዙም አይመችም። ”አይዞህ፥ ነስሩዲን! አታልቅስ፤ ቤት እስክትገባ በጥሩ ሁኔታ እይዝሃለሁ፥ ነስሩዲን። ነገሮች በጥሩ ሁኔታ ይቆያሉ-አንተ ረጋ ካልክ።” እያለ ያባብለዋል። አንድ እናት-መሳይ ሴትዮ አጠገቡ ቆማ ነበር፤ አውቶብስ እየጠበቀች። ”የልጅ እንክብካቤን ጥንቅቅ አድርገህ ታውቃለህ፤ በጣም ደስ ይላል።” ከዛ አንገቷን ወደህጻኑ አስግጋ፥ ”አታልቅስ፥ ነስሩዲን! ሁሉም ነገር በጥሩ ሁኔታ ይሄዳል። ”

“ሴትዮ!” አባትዬው ባረቀ፥ ”ነገሮችን ወደአልተፈለገ አቅጣጫ እያስቀየስሻቸው ነው። የኔ ስም ነስሩዲን ነው፤ የልጄ ደግሞ ቶማስ። ተሳስተሻል! ”

⁜⁜⁜

• ሾፌር አልባ መኪና

ሙላ ነስሩዲን ባለሁለት ወለል አውቶብስ ላይ ተሳፈረ። መጀመሪያ የገባው የላይኛው ወለል ላይ ነበር። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ፥ ነስሩዲን እየተንደረደረ ወረደ፤ በንዴት እያጉተመተመ።

“ችግር አለ?” ሾፌሩ ጠየቀ።

“የላይኛው ክፍል አስተማማኝ አይደለም፤ ምክንያቱም ምንም ሾፌር የለም። ”

⁜⁜⁜

- **የክብር ደረጃ**

“እኔ እንደዚህ መሆኑን አልገምትም። ደግሞም ምንም የማሰማው አቤቱታ የለም። ” አለ፥ አንድ ነገር-ሁሉ የተዘበራረቀበት ወጣት። ሙላ ነስሩዲን የልጁን ንግግር እንደሰማ፥ ወዲያውኑ ከጭፈራ ቤቱ እንዴት አድርጎ ዘበኛው እንዳባረረው መናገር ጀመረ፥

“በጥሩ ሁኔታ ነበር ያስወጣኝ። ”

“ምን ማለትህ ነው? በጥሩ ሁኔታ ነው ያስወጡህ?” ጠየቀ፥ ወጣቱ፥ ”ከጭፈራ ቤቱ በግፍ አላስወጣኸም? ”

“አስወጥቶኛል!” መለሰ፤ ነስሩዲን፥ ”በኋላ በር አስወጣኝ። ግን ለጭፈራ ቤቱ ዘበኛ ቤተሰቦቼ በመንግስት እርዳታ እንደሚኖሩ ስነግረው፥ እንደገና-በአክብሮት-በፊት በር መርቶ፥ ከጭፈራ ቤቱ አስወጣኝ። ”

፡፡፡፡፡

- **ከድርቆሹ ስር**

ወጣቱ ሙላ ነስሩዲን በመኪናው ጀርባ የድርቆሽ ክምር ጭኗል፤ ውስጡ በብስጭት ተሞልቷል። ይሄኔ አንድ ቀና ገበሬ ለሙላ ነገሮችን ረስቶ፥ መንፈሱን እንዲያረጋጋ ምክር-ቢጤ ይለግሰዋል-መክሰስም ከርሱ ጋር አብሮ እንዲመገብም። ”መኪናህንም በደንብ እናስተካክላታለን!” ሲል፤ ምክሩ ላይ አከለበት። ሙላ አባትዬው ነገሩን ቢያውቅ፥ ነፍሰ-ሲጋውን እንደሚደመስሱበት ለገበሬው ነገረው። ”አይ! ...አትጨናነቅ!” በሙሉ ተስፋ፥ ”ሁሉም ነገር ጥሩ ይሆናል።” እናም፥ ነስሩዲን ራት ከገበሬው ጋር አብሮ ተመገበ። ከቆይታ በኋላ፥ ሙላ ጥሩ ስሜት እንደተሰማው ከምስጋና ጋር ገለጸ። ”ግን...” አለ፤ ሙላ፥ ”እስካሁን ግን አባቴ ነገሩን ‹ቢሰማስ? › ብዬ እያሰብኩ ነው። ”

“እርሳው’ባክህ!” የቅድሙን ቃል ገበሬው ደገመ። ”በነገራችን ላይ! አባትህ የት ነው ያለው? ”

“ከድርቆሹ ስር!” መለሰ፤ ነስሩዲን።

⁘⁘⁘

• ኮተለክሁ

ሙላ ነስሩዲን በአካባቢው የሚገኘው መጋዘን ለመቀጠር፥ ማመልከቻ አስገባ። ጓደኛው እንደነገረው ከሆነ፥ በድርጅቱ ህግ መሰረት፥ ካቶሊክ ያልሆነ ሰው አይቀጠርም፤ ስራውን በጣም ከፈለገው፥ ዋሽቶ መቀጠር ግን ይቻላል። ስለዚህ ሙላ “ካቶሊክ ነኝ!” ብሎ ሊዋሽ ተሰናዳ።

ነስሩዲን አመለከተና ለቃለ-መጠይቅ ፈተና ተጠራ፤ ሰውዬው የተለመዱ ጥያቄዎችን ጠየቀው-እርሱም መለሰ። ወደ መጨረሻ አካባቢ፥ ”የየትኛው ቤተ-ክርስቲያን አማኝ ነህ?” ሲል፥ ጠየቀው።

“እኔ ካቶሊክ ነኝ!” መለሰ፤ ነስሩዲን፥ ”ቤተሰቦቼ በሙሉ ካቶሊክ ናቸው። በውነቱ፥ አባቴ ካህን ነው፤ እናቴ ደግሞ መነኩሲት! ”

⁘⁘⁘

• ወርቃማ ዓሳን ማመስገን

ጓደኛው እንዲህ ሲል ይጠይቀዋል፥

“ሙላ! የቤትህ አስተዳዳሪ ማነው? ”

“ጥሩ...” አለ፤ ነስሩዲን፥ ”ሚስቴ ልጆቼን፥ ሰራተኞችን፥ ውሻውንና በቀቀኑን ታስተዳድራለች። ግን በትንሹ ወይም በጥሩ መልኩ የዘረዘርኩልህ ሹመት-ልክ ወርቃማ አሳ እንደማመስገን ቁጠረው። ”

⁘⁘⁘

• ጭማሪ እንክብካቤ እሳቤ

ሙላ ነስሩዲን ስራ ለመቀጠር አንድ ድርጅት አመለከተ።

“ድርጅቱ ብታመም፥ የመታከሚያ ገንዘብ ይሰጠኛል?” ብሎ ጠየቀ፤ ነስሩዲን።

“አይሰጥኽም፤ ራስህ ነህ የምትከፍለው።” የሰው ሃይል አስተዳደሩ መለሰ። ”ከደሞዝህ በየወሩ ይቆረጣል። ”

“ከዚህ በፊት የሰራሁበት መስሪያ ቤት ሙሉበሙሉ ወጪውን ሸፍኖልኛል። ”

“ያልተለመደ ነው።” በግርምት ተናገረ፥ ”የዓመት ፈቃድ ለምን ያህል ጊዜ ሰጡኽ? ”

“ለስድስት ሳምንት!” መለሰ፥ ሙላ።

“ጭማሪ አግኝተሃል? ”

“አዎ!” መለሰ፤ ነስሩዲን፥ ”እርሱ ብቻ ኣይደለም። በየዓመቱ ከደሞዛችን ሌላ ጭማሪ ገንዘብ ይከፈለናል፤ የምሰጋና ቀንን እንድናከብር ወደቱርክ ይሰድዱናል፤ የድርጅቱን መኪና እንድንጠቀም ይፈቅዱልናል፤ በጋራ ስጋ ጠብሰን እንበላለን- በየዓመቱ። ”

“ታዲያ! ለምን ለቀቅኽ?” ጠየቀ፤ አስተዳደሩ።

“ባለቤቶቹ ታሰሩ! ”

⁘⁘⁘

• ጥቂት ሃብት

የከተማይቱ ዲታ ማረፉ ተነገረ። በነጋታው አንድ ሃብታም ሽማግሌ፥ በስግብግብነቱ የሚታወቅ፤ ከነስሩዲን ጋር አፍለአፍ ገጥሞ ያወራል፥

“የተወው ሃብት ብዛቱ የትየለሌ ነው፤ ይገርማል! ”

ሙላ ነስሩዲን ከት ብሎ ሳቀና፥ ”እያንዳንዱን-ቅንጣት ሳንቲሙን እኮ ነው ትቶት የሄደው፥ ጌታው! ”

⁘⁘⁘⁘

• ደንበኛ ስራ

አንዲት ወይዘሮ ሙላ ነስሩዲንን፥ ”ስራ-ደንበኛ ስራ ሰርተኽ ታውቃለህ?” ስትል፥ ጠየቀችው፤ በሩ ደፍ ላይ ቆማ።

“አንድ ጊዜ ብቻ ነው የሰራሁት፥ እህቴ!” አለ፤ ነስሩዲን፥ ”ከበሩ በስተጎን ቆሜ ያለምንም እርባና ከአንዲት ሴት ጋር አውርቼያለሁ፤ ትንሽ ትህትና ካ’ላት ጋር። ”

⁘⁘⁘⁘

• አዲስ ነገር

ሙላ ነስሩዲን ወደአንድ የታወቀ ሆቴል፥ የምኽታ ክፍል ለመያዝ ዘለቀ።

“እንኳን ደህና መጣህ!” አለ፤ እንግዳ ተቀባዩ፥ ”እንኳን ደህና መጣህ! ሁሉም ነገር ላ’ንተ በሚመችና በሚስማማ መልኩ እናዘጋጃለን፤ የቤትህ ያኽል እንዲሰማህ እናደርጋለን። ”

“እባክህ! እንደ’ሱ አትበል!” አለ፤ ሙላ፥ ”ቤት ለቅቄ ወደ’ዚህ የመጣሁት የለውጥን አየር ለመተንፈስ ነው። እኔ ምፈልገው፥ እዚህ በምከርምበት ወቅት፥ ሆቴሉ እንደቤቴ ሳይሆን እንደ አንድ-የባህር ዳርቻ ላይ እንደሚገኝ የመዝናኛ ቦታ እንዲሰማኝ ነው። ”

⁘⁘⁘

• ዛቻ አጣጣል

ዳኛው ሙላ ነስሩዲንን እየጠየቁ ነው።

“ሚስትህ የመግደል ዛቻ ሰንዝራብሃለች።” ተናገረ፥ ዳኛው።

“ልክ ነው፥ ክቡር ዳኛ!” መለሰ፥ ነስሩዲን።

ዳኛው አንገቱን አሰገገና በሙላ ጆሮ ስር አንሿኩከ፥ ”አንዱ አንተ ላይ ዛቻ ቢጥልብህ! ምንድነው የምታደርገው? ”

⁘⁘⁘

• የጥበብ ግርምታ

ሙላ ነስሩዲን ከመምህሩ ጋር እያወራ ነው፤ ከስዕል መምህሩ ጋር።

“ሁልጊዜ አንተ ከሳልካቸው ስዕሎች አንዱን ስመለከት፥ በጣም እደነቃለሁ፤ ቆሜ ማጨብጨብም ያምረኛል። ”

“እንዴት ልትገረም ቻልክ?” በግርምታ፥ መምህሩ ጠየቀ።

“አይ! …” አለ፤ ነስሩዲን፥ ”ለምን እንደሳልከው ሊገባኝ ስላልቻለ፤ ይገርማል! ”

፨፨፨፨

• ስራ የማግኛ መላ

አንድ አይታወቄ ሰው ሙላ ነስሩዲንን መንገድ ላይ አቆመው፤ ሳንቲም ለመለመን።

“ጸጉርህን ከተስተካከልክና ገላህ ከተጣጠብክ፥ ወዲያውኑ ስራ ታገኛለህ።” ይለዋል።

“ልክ ነህ!” ሙላ ተናገረ፥ ”አንተ እንዳልከው ባደርግ ኖሮ፥ ስራ እንደማገኝ ያወቅኩት፥ ከዓመት በፊት ነበር። ”

፨፨፨፨

• ዕብዱን መፈለግ

ሙላ ነስሩዲን ወደአንድ የአዕምሮ ህክምና ሆስፒታል አምርቶ፥ የዘቦች ሃላፊውን አስጠራ። ከተገናኙ በኋላ፥ እንዲህ ሲል ጠየቀው፥

“ከሆስፒታላችሁ ያመለጡ ወንድ ህመምተኞች ነበሩ? ”

“ለምን ጠየቅኸኝ?” ዘቡ በኮስታራ ድምጹ ጠየቀ።

“ምክንያቱም አንድ ከእናንተ ያመለጠ ህመምተኛ፥ ከሚስቴ ጋር አንሶላ ሲጋፈፍ አጅከፈንጅ ይገፍዋለሁ። ”

፨፨፨፨

• የባከነ ዕድል

ሙላ ነስሩዲን የተሰበረ እግሩን አቅፎ፥ ያ’ረጀች መኪናው ውስጥ ጋለል ብሏል። ነዳጅ ቀጂው ነስረዲንን ይጠይቃል።

“እግብተሃል? ”

“አላገባሁም።” መለሰ፥ ”ካባከንኳቸው ነገሮች የሚቆጨኝ ይህ ነው፤ አለማግባቴ። ”

፨፨፨፨

• ምክርና ገንዘብ

ሙላ ነስሩዲን ወደአንድ “ጨዋ” ወደተባሉ ሽማግሌ ቤት ሄደ፤ ምክር ፈልጎ። ሰውዬው ተረትና ምሳሌን በምክራቸው እየለገሱ ይናገራሉ። ነስሩዲን ግን ከምክር በላይ ገንዘብ ፈልጎ ነበርና ጠየቃቸው። ሽማግሌው በእምቢታ መንፈስ፥ ”ይቅርታ፥ ልጄ! እኔ ምንም ገንዘብ የለኝም። ግን ከገንዘብ የሚልቁ ምክሮችን ልቸርህ እችላለሁ። ”

ሙላ ምክር ባልፈለገ አንደበት፥ ”አልፈልግም፤ እግዜር ይስጥልኝ። ምንም ገንዘብ ካልሰጡኝ፥ ምክርዎ ብቻውን አይጠቅምም።” አላቸው።

፡፡፡፡፡

• የብድር ጓደኝነት

“እጄን ተሰብሬ በነበረበት ወቅት” ሙላ ነስሩዲን ለጎረቤቱ ሲያወራ፥ ”...አንድ በጎ ፈቃደኛ ወጣት 1000 ብር ላበድርህ ብሎኝ ነበር። ”

“ተቀበልከው? ”

“አልተቀበልኩም፤ በብድር የሚመጣ ጓደኝነት ለመለያየት በጣም ቅርብ ነው። ”

፡፡፡፡፡

- **ሁለቱ በረራዎች**

ወጣቱ የአውሮፕላን አብራሪነቱን ፈተና ተፈትኖ አለፈ። ብቃት እንዳለው ለማሳየት፥ ሙላ ነስሩዲንን አግባብቶ በአውሮፕላኑ አሳፈረው። ሙላም አብሮ ከልጁ ጋር አየር ላይ ተንሳፈፈ። ወደምድር እንዳረፉ፥ ሙላ ልጁን እንዲህ አለው፥

“ስለሁለቱ ጉዞዎች በጣም አመሰግንሃለሁ!”

“ስለሁለቱ ‹ጉዞዎች› ስትል? ምን ማለትህ ነው፥ አጎቴ?” ሲል፤ ጠየቀ። ”ደግሞ አንድ ጊዜ ነው የበረርነው።”

“አይደለም፤ ሁለት ነው። አንደኛው መነሻችን ላይ፥ ሌላኛው ደግሞ መድረሻችን ላይ!”

⁜⁜⁜⁜⁜

• የተያዥ ትዝታ

የቤት እመቤቲቱ ለሙላ ነስሩዲን “ሳንድዊች” ሰጠችው፤ አንድ ጥያቄም ጠየቀችው።

“ስራ ማግኘት አልቻልክም? ”

“አዎ፥ እመቤቴ። ያለው ስራ በጣም አነስተኛ ነው።” አለ፤ ነስሩዲን፥ ”ሁሉም አሰሪዎች ተያዥ ይፈልጋሉ፤ ለመቀጠር። ”

“ተያዥ አላገኘኽም? ”

“አላገኘሁም፤ ደግሞም ተያዤ ከሞተ ሃያ ዓመት አለፈው። ”

፨፨፨፨

• ስብከቱ

ሙላ ነስሩዲን ምዕመናንን እንዲሰብክ በካህናቱ ተጋበዘ፤ እርሱም ግብጥውን ተቀብሎ፥ አትሮንሱ ላይ ተሰየመ። መጀመሪያ ያደረገው ነገር፥ ታዳሚያኑን ጥያቄ መጠየቅ ነበር።

“ዛሬ የማሰማችሁን ትምህርት አስቀድማችሁ ታውቃላችሁ? አታውቁም? ”

“አናውቅም” ምዕመናኑ መለሱ።

“ካላወቃችሁማ፥ ለምን አስተምራችኋለሁ? !” ብሎ፥ ከዓውደ-ምህረቱ ወረደ።

ታዳሚው በዕፍረት ዱላ ተመታ።

አንዲሁ፥ በሌላ ቀን ጋበዙትና አትሮንሱ ጋ ተከሰተ፤ ባለፈው የጠየቃቸውን ጥያቄ ደግሞ ጠየቀ።

አማንያኑ ከባለፈው ስህተታቸው ትምህርት ወስደው፥ ”አዎ፤ እናውቃለን!” ሲሉ መለሱ።

ነስረዲንም፥ ”ካወቃችሁማ፥ እኔ ምን አለፋኝ!” ብሎ፥ አንደገና ከዓውደ-ምህረቱ ወረደ።

ምዕመናኑ ግራ ተጋቡ።

በሚቀጥለው ሳምንትም ጋበዙት፤ እርሱም ጥያቄውን ደገመ።

አንደኛው ጎራ፥ ”አዎ!” ሲል፤ ሌላኛው ጎራ ደግሞ “አናውቅም!” አለ።

መልስ የማያጣው ነስሩዲንም፤ እንዲህ ሲል አዘዛቸው፥

“እናንተ-የምታውቁት! ለማያውቁት ወንድሞቻችሁ አስተምሩ! እኔ በከንቱ አልደክምም! ”

⁞⁞⁞⁞

- **ማንን ነው የምታምነው?**

ጎረቤትዬው ሙላ ነስሩዲንን ለማግኘት ወደሙላ ግቢ ዘለቀ፤ ሙላም እርሱን ለማናገር ወደውጭ ወጣ።

“ሙላ! አህያህን ለተወሰነ ጊዜ ልታውሰኝ ትችላለህ? ”

ሙላ ነስሩዲንም አህውን ማዋስ አልፈለገምና እንዲህ ሲል መለሰለት፥

“ይቅርታ! አህያውን ሌላ ሰው ወስዶታል! ”

ይሄኔ አህያው ከታሰረበት በሃይለኛው ጮኸ።

ሰውዬውም በ”አገኘሁ” ስሜት፥ ”ሙላ! አህያውኮ እየጮኸ ነው! እዚሁ ነው!” አለ።

“መልስ በኪሱ” የሆነው ሙላ ሰውዬውን እንዲህ ሲል ጠየቀ፥

“ከአህያውና ከኔ-ከሙላ ማንን ነው የምታምነው? ”

⁘⁘⁘

• አብርሆት

ነስሩዲን በብዙ ተከታዮቹ ታጅቦ፥ አንድ የንግድ ባዛር ውስጥ ይንቀሳቀሳል። ተከታዮቹ እርሱ የሚከውነውን ማንኛውንም ነገር ያደርጋሉ። ነስሩዲን ሲቆም ይቆማሉ፤ ሲያስነጥስ አብረው ያስነጥሳሉ፤ እግሩን ከመሬት ጋር እያፋጨ፥ እጁን ወደሰማይ እያውለበለበ ሲጮህ፥ ተከታዮቹም ተመሳሳዩን ይተገብራሉ።

አንድ ሸማች ነስሩዲንን “ሰላም” ካለ በኋላ፥ ”ተከታዮችህ ያንተን ድርጊት እየተከተሉ የሚተገብሩት ለምንድነው?” ብሎ ጠየቀው።

“የሱፊ ሸኽ ልሆን ነው።” ሲመልስለት፥ ”እነዚህ የኔ መንፈሳዊ ተከታዮች ናቸው፤ አብርሆትን ማግኘት ይሻሉ። አብርሆትን እንዲያገኙ ደግሞ፥ እኔ በደንብ አግዛቸዋለሁ። ”

“አዕምሯቸው በትክክል እንደሚያስብና እንደበራ፥ አንተ እንዴት ታውቃለህ?” ደግሞ ጠየቀው።

“ቀላል ነው። በየጠዋቱ የተከታዮቼን ብዛት አያለሁ። ከተከታዮቼ መካከል አንዱ ቢጎድል፥ ለጠፋው ሰው አብርሆቱ ተገልጧል ማለት ነው። ”

⁘⁘⁘⁘

• ቀለበቱ

ሙላ የጣት ቀለበቱ ጠፍቶበታል፤ ከተቀመጠበት ሳሎን ቢፈልግ-ቢፈልግ ያጣዋል። ወደጓሮውም ወጣ አለና መፈለጉን በብርቱ ተያያዘው። ሚስቱም ብቅ ብላ፥ ፍለጋውን በአንክሮ ትመለከታለች። የቀለበቱን መጥፋት አውቃለች፤ የጠፋበትም ሳሎን ተቀምጦ በነበረበት ጊዜ መሆኑን ጠንቅቃ ተረድታለች። እናም፥ ሙላን ጠየቀችው፥

“ሙላ! ቀለበቱ የጠፋብህኮ ሳሎን ውስጥ ነው። ለምን ጓሮ ውስጥ ወዲያ-ወዲህ ትላለህ? ”

ሙላም ጉሮሮውን ሞራረደና፥ ”ሳሎን ውስጥ ያለው ብርሃን በጣም የደከመ ነው። ይህ ደግሞ ለዓይኔ ጥሩ አይደለም። ጓሮ ብወጣ ግን በቂ ብርሃን ስለማገኝ፥ ፍለጋዬን በጥሩ ሁኔታ አካሂዳለሁ። በዚህ ምክንያት ነው-ደጅ ወጥቼ ቀለበቴን እምፈልገው።” ሲል መለሰላት።

⁞⁞⁞⁞⁞

• ተርፈ.ያለሁ

“ሽርሽር ወጥተን በነበረበት ወቅት፥ በዓለም ውስጥ ምን ተፈጽሞ ነበር?” አንደኛው ጓዱ ጠየቀው፥ ”ደግሞ በየመጠጥ ቤቱ ስትንገላጀጅ ‹ነበር› አሉ። ”

“ጥሩ፥ እኔ ጅል አይደለሁም!” አለ፤ ሙላ፥ ”ጥቂት ሴቶች የተርብ ጎጆ ዛፍ ላይ አግኝተው እንዳወርድላቸው ጠይቀውኝ ነበር። እኔ ግን ‹እምቢ› አልኳቸው። ”

“በጣም አስተዋይ ነህ!” ጓደኛው ተናገረ፥ ”አንዳንዴ የምትሰራቸው ነገሮች፥ ያ’ንተን ስም በጎ ባልሆነ መልኩ እንዲነሳ ያደርጋሉ። ”

“ልክ ነህ፤ ግን እኔ በተርቡ አልተጎዳሁም-አልተነደፍኩም። ”

፨፨፨፨

• አፍቅሮት-ዶሮ ጥብስ

የሙላ ነስሩዲን ሚስት ባሏን እንዲህ ስትል ጠየቀችው፤ የራት ግብዣ ላይ፥

“አሁን ላ’ምስተኛ ጊዜ ዶሮ ጥብስ ለማንሳት ወደቡፌው ሄድክ። ትንሽ አያሳፍርኽም? ”

“አላፍርም!” መለሰ፤ ነስሩዲን፥ ”ለዶሮ ጥብሶቹ እኔ ለ’ነርሱ እንደተገባሁ እየነገርኳቸው ነው። ”

፨፨፨፨

• ጉጉቱ

ሙላ ነስሩዲን ተዳሪውን ሙሽራ በጠለቀ ስሜት ጨበጠው።

“እንኳን ደስ ያለህ፥ ጓዴ!” አለ፤ ሙላ፥ ”ከደስታ ቀናትህ፥ ይኸኛው አንዱ ነው። ”

“ግን እስከነገ ድረስ አልዳርም።” የወደፊቱ ባል ተናገረ።

“አውቃለሁ! ጉጉቱ ራሱ’ኮ የሚጥም ደስታ ነው። ”

፡፡፡፡፡

• ፍርጠጣ

ሙላ ነስሩዲንና ሚስቱ በቅርቡ ስለተከሰተው የጋብቻ ቅሌት የጦፈ ሃሜት ላይ ናቸው።

“አስበው አስኪ....” አለች፤ ሚስቲቱ፥ ”ሙሽሪት በመተላለፊያው ኮሪደር እየመጣች በነበረችበት ሰዓት ነው-ሙሽራው ከቤተስኪያኑ ‹እግሬ አውጪኝ› ብሎ የመረሸው። አቅሉን ስቶ መሆን አለበት። ”

“አይ! እኔ እንደዚህ አይመስለኝም። በግድ ሊያገባ እንደሆነ ከዘገዬ አወቆ ነው የፈረጠጠው። ”

፡፡፡፡፡

• አስክሬኑ

“አባዬ...አባዬ!” ልጅቱ እያለቀሰች፥ ”የሆነ ሬሳ ከጣሪያው ወድቋል። ”

“አውቃለሁ፥ የኔ ልጅ!” አለ፤ ሙላ ነስሩዲን፥ ”የወደቀው አስክሬን በመስኮት በኩል ሲገባ አይቼው ነበር። ”

⁘⁘⁘

• ምርጫ

የምርጫው ሂደት በተሸናፊው-በሙላ ነስሩዲን እየታወከ ነው።

“ምርጫው ተጭበርብሯል። የኔ ጓደኛ 15 ጊዜ ድምጹን ሰጥቶኛል፤ ቀበሌ3 የሚገኘው ጣቢያ ላይ። ግን ከ15ቱ የደረሰኝ አራቱ ብቻ ነው። ”

⁘⁘⁘

- **ምርጫ**

የምርጫ ተወዳዳሪዎች ለህዝቡ የቅስቀሳ ንግግር እንዲያቀርቡ ዕቅድ ተይዟል፤ ሁሉም በጋራ ነው የሚያቀርቡት። ተወዳዳሪዎቹን ለማስተዋወቅ የተመረጠው ሙላ ነስሩዲን ነው።

መድረኩ ላይ ወጣና፥ ”አሁን የሚናገረው ተወዳዳሪ ለሃገራችን ያለው ምኞት ሰናይ፥ ያለው ፍቅር የላቀ ነው። ሁላችንም ከተንከሲስ አደጋዎች ይጠበቀናል። ካለ በኋላ፤ አንገቱን ወደተወዳዳሪዎቹ አዙሮ፥ ”ከእናንተ መካከል መናገር የሚፈልግ እጁን ያውጣ! ”

⁞⁞⁞⁞⁞

• አስጠባቂው

ሙላ ነስሩዲን በተሳፈረበት አውቶብስ ቀርፋፋነት በጣም ተማርሯል፤ ምሬቱን ለሾፌሩ እያራገፈ ነው። ሾፌሩም ታክቶት፥ ”ቀርፋፋ መሆኑን ካወቅክ፥ ለምን ወርደኽ በእግርህ አትሄድም?” ይለዋል።

ሙላም፥ ”እችል ነበር። ግን ሚስቴ እኔን እየጠበቀች ነው፤ አውቶብሱ እስከሚደርስ እርሷ በደንብ ቆማ እንድትጠብቀኝ ፈልጌ ነው። ለዚህ ነው-በእግሬ የማልሄደው። ”

፨፨፨

• ፉክክር አልባ

ለከተማው አዲስ የሆነ ሰው፥ ከሙላ ነስሩዲን ጋር ይገናኛል።

“እዚህ የመጣሁት ጥሩ የሆነ ኑሮ ለመኖር ነው።” ይላል፤ አዲሱ ሰው።

“ጥሩ፤ እንዳልከው መኖር ትችላለህ። ምክንያቱም ምንም የእርስበርስ ፉክክር የለምና።” አለ፤ ሙላ ነስሩዲን።

፨፨፨

- **መደበል**

ሙላ ነስሩዲን ወደአንድ መጠጥ ቤት እየተጣደፈ ሄደ።

“የተለመደውን...አፍጥነው፥ ወንድም! ባቡሩ እንዳያመልጠኝ! ”

ባሬስታው አምስት “ማርቲን” በረድፍ አሰልፎ ሰጠው። የመጀመሪያውንና የመጨረሻውን መለኪያ ትቶ፥ ሁለተኛውን-ሶስተኛውንና አራተኛውን ባ’ንድ ትንፋሽ፥ በየተራ ጨለጣቸው። ወዲያውኑ በመጣበት ፍጥነት እየካለበ ወጣ።

አንዱ ታዛቢ ባሬስታውን ለምን ሙላ ሁለቱን ትቶ እንደወጣ ይጠይቃል።

“ሁልጊዜ እንደዚህ ያደርጋል። የሚናገራት አንድ የተለመደች አባባል አለች። ‹የመጀመሪያው ምንጊዜም ይጥማል፤ በጣም። የመጨረሻው ደግሞ ችግር ይፈጥራል። ምክንያቱም ቤት ሲሄድ፥ ጥንብዝ ብዬ ሰክሬ ሊሆን ነው። ”

፡፡፡፡፡

• አስታዋሿ

ሙላ ነስሩዲን ሚስቱን ከጓደኛው ጋር ሆኖ እያማ ነው።

“ለ’ርሷ ስል፥ ምን እንደምሆን አላውቅም።” አለ፤ ነስሩዲን፥ ”በዚህ ዓለም የሚያስጠላ አዕምሮ ያላት እርሷ ብቻ ሳትሆን አትቀርም። ”

“ብዙ ነገር ትረሳለች ማለት ነው?” ጠየቀ፤ ጓደኛው።

“ሂሽ! አይደለም። ሁሉንም ነገር ታስታውሳለች፤ ትንንሽ ድርጊቶችን ሳይቀር። ”

፨፨፨፨

• ኢንሹራንስ

“ኢንሹራንስ በዓለም ላይ ካሉ ወሳኝ ነገሮች አንዱ ነው።” አንድ ተግቶ የሚሰራ የኢንሹራንስ ሻጭ ለደንበኛው-ለሙላ ነስሩዲን ይነግረዋል፥ ”ስለዚህ 75,000 ሩፒ ለአንተ የህይወት ዋስትና ተቀማጭ ይሆንና በምታርፍበት ወቅት ለሚስትህ ገንዘቡ ይሰጣል። ”

“በነገራችን ላይ፥ የኔ መኖር ምን ያህል አንጠብቂችኋል?” አለ፤ ነስሩዲን።

፨፨፨፨

• የዕይታ ዶክተር

“ዶክተር!” አለች፤ አንዲት ሴትዮ፥ የሙላ ነስሩዲን ቤት እየተጣደፈች ስትዘልቅ። ”አንድ ነገር በርግጠኝነት እንድትነግረኝ እፈልጋለሁ። ምን ዓይነት በሽታ ነው ያለብኝ? ”

ነስሩዲን ከእግር ጥፍሯ እስከ ራስ ጠጉሯ ተመለከታትና፥ ”እመቤቴ! ሶስት ነገሮችን ልንገርሽ! የመጀመሪያው በጣም ወፍራም ነሽ። ሁለተኛ የውበትሽ ደረጃ ከፍ ሊል ይችላል፤ የከንፈርና የጉንጭ ቀለም መቀባት ከተውሽ። ሶስተኛ አኔ ዶክተር አይደለሁም። አስፋልቱን እንደተሻገርሽ ክሊኒክ ታገኛለሽ። እዛ ታከሚ! ”

⁘⁘⁘

• ባገኝ ኖሮ

ሙላ ነስሩዲን ቀኑን ሙሉ አሳ ሲያጠምድ ውሏል። አንድ በ’ርሱ በኩል የሚያልፍ ሰው-በሁኔታው ይገረምና-ቆሞ ይጠይቀዋል።

“ምን ያህል አሣ አጠመድክ፥ ሙላ?” ሲል፤ ጠየቀው።

“ይኸኛውን-ሽራፋውን ባጠምድና ሌሎች-ሁለት አሳዎችን ባጠምድ፥ ሶስት ይሆኑልኝ ነበር። ”

⁘⁘⁘

• አስተውሎት

ሙላ ነስሩዲን ወደጠበቃው ቢሮ አመራ፤ የፍቺ ውሉን ለማሰር።

“ለፍቺ ያነሳሱህ ዋና-ዋና ምክንያቶች ምንድናቸው?” ጠየቀ፥ ጠበቃው።

“ሚስቴ የምታደርጋቸው ነገሮች ናቸው፤ ምክንያቶቼ።” ነስሩዲን፥ ”የጠረጴዛ አቀማመጧ በጣም ያስጠላል። የቤተሰቤን ክብር ያዋርዳላ! ”

“ነገሩ ያሳዝናል።” ጭንቅላቱን እየወዘወዘ፥ ”ከተጋባችሁ ምን ያህል ጊዜ ይሆናችኋል? ”

“ዘጠኝ ዓመት! ”

“ለዘጠኝ ዓመት ሙሉ የጠረጴዛው አኳኋን አስጠላህ፤ ይሁን! አሁን ግን ለመፋታት የተነሳህበት ምክንያት አልዋጥልህ ብሎኛል። ”

“ጥሩ፥ ነገሩን ከዚህ በፊት አላስተዋልኩትም ነበር። የቤት አያያዝ መጽሃፍ ካነበብኩ በኋላ ዝርክርክነቱ ታየኝ። ”

⁘⁘⁘

• ወይኔ አለመቅመሴ!

ሙላ ነስሩዲን ለሚስቱ ትናንት ማታ ስላለመው ህልም እየተናገረ ነው።

“በጣም ያስደነግጥ ነበር።” ሲጀምር፥ ”እነዮሃንስ ቤት እንድ የልደት በዓል ዝግጅት ተሰናድቶ ነበር። የዮሃንስ እናት የቸኮሌት ኬክ አዘጋጅች-10 ጫማ ቁመት ያለው። ሲቆረስ የሚኖረው ርዝመት ደግሞ የትየለሌ ነው። በስሃን ስንይዘው በጣም ይከብደን ነበር። በዚያ ላይ ቤት ውስጥ ያዘጋጀችውን ‹ክሬም› አድርጋበታለች። ከማድረጉ በተጨማሪ፥ በርሜል ሙሉ ‹ክሬም› ከጎናችን ተቀምጧል፤ እየጨለፍን እንድንጠጣው። ”

“የቱ ነው-በጣም ያስደነገጠህ?” ጠየቀች፤ ሚስት።

“ከሬሙን ሳልቀምሰው መንቃቴ ነበር-በጣም ያስደነገጠኝ። ”

⁘⁘⁘

• እንዳንተ ብሆን

መጠጥ ቤቱ ውስጥ የቀለጠ ጨዋታ ነበር። ሙላ በጣም ሰክሮ ስለነበር፥ በጓደኞቹ ታዝሎ ወጣ። በነጋታው ሲነቃ፥ አጠገቡ ዕደሜው 45 የሚሆን ጦጣ ተኝቷል። ነስሩዲን በአተኩሮት ጦጣውን ተመለከተና፥ ”እወነተኛ ጦጣ ብትሆን ኖሮ፥ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ትኖር ነበር፤ በጥሩ ሁኔታ ውስጥ ብትኖር ደግሞ፥ እኔን ትሆን ነበር። ”

፡፡፡፡፡

• ግዴታ የለብሽም!

ነስሩዲን ሚስቱን፥ ”ውዴ! የቤተሰብ ህጉ ‹ሴት ልጅ ከወንዱ በበለጠ መተኛት አለባት። › ይላል።” አላት።

“ህጉ ትክክል ነው’ንዴ?” ሚስት ጠየቀች።

“ትክክል ነው፤ ውዴ።” አለ፤ ሙላ፥ ”ስለዚህ እኔን እስከ ዕኩለ-ሌሊት መጠበቅ የለብሽም። ”

፡፡፡፡፡

- **ዕምነቴን አስወግድ!**

ሙላ ነስሩዲን የስነ-ልቦና ባለሙያ’ጋ ሄደ፤ ችግሮች እንዳሉበትና እርዳታ እንደሚፈልግ ነግሮ፥ ከባለሙያው ፊትለፊት ተቀመጠ።

“ላዋራህ ፈልጌ ነበር።” ተናገረ፤ ሙላ፥ ”መርሆቼ ከህሊናዬ ጋር እየተጋጩ ነው። በጣም ያስቸገረኝ ግን ህሊናዬ ነው። ”

“ገባኝ! በራስ የመተማመን ሃይልህን ለማሳደግ ፈልገኽ ነው-ወደ’ኔ የመጣኽው? ”

“አይደለም። እንደ’ርሱ አይደለም የፈለግኩት። የራስ መተማመኔን ከቻልክ እንድታዳክምልኝ ነው የመጣሁት። ”

⁞⁞⁞⁞⁞

• ምርጫ

ሙላ ነስሩዲን በባለፈው ምርጫ በአብላጫ ድምጽ ተሸነፈ። ክፉኛ ጸጸት ልቡን አናጠበበት።

“ተጠቂ ነበርኩ። ምንም አልሆንኩም። ግን ተጠቂ ነበርኩ። ”

“ተጠቂ?” ጠየቀ፤ አዳማጭ ጓደኛው፥ ”ተጠቂ የሆንከው በምን መልኩ ነው? ”

“በትክክል ድምጹ ስለተቆጠረ፥ ተጠቂ ሆንኩኝ።” መለሰ፤ ነስሩዲን።

፡፡፡፡፡

• እንቅልፍም እንደአስተያየት

አንድ ወጣት ጽሃፌ-ተውኔት ሙላ ነስሩዲንን ጋበዘ፤ ቴአትሩን እንዲያይለት።

ሙላም እንደተጋበዘው መጣና ወንበር ላይ ተዘርፍጦ፥ እንቅልፉን መለጠጥ ጀመረ። እርሱ የጠለቀ ህልም በሚያልምበት ሰዓት፥ የቴአትሩ ትዕይንት እየነጎደ ነበር። ጽሃፌ-ተውኔቱ ተናደደና፥ ”ሃሳብህን-ዕይታህን ምን ያህል እንደምፈልገው እያወቅክ፥ ለምን ትተኛለህ?” ሲል፤ ይጠይቀዋል።

ሙላም፥ ”ልጄ! እንቅልፍ ራሱ አንድ አስተያየት ነው።” ብሎ፤ መለሰለት።

ፈፈፈፈ

• ከብትና ፈረስ

“በጣም የምታስቅ ላም ናት!” አንድ ትውልዱ ከወደከተማ የሆነች ልጅ። የተናገረቸው ለሙላ ነስሩዲን ነበር። ”ብዙ ምክንያቶች አሉ።” ነስሩዲን፥ ”ለምን ላም ቀንድ እንደሌላት አንድ ምክንያት ይኖራል። አንዳንዶች እስከዕለተ-ሞታቸው የማያበቅሉ አሉ። አንዳንዶቹ ቀንድ-አልባም ይሆናሉ። ሌሎቹ ደግሞ ቀንድ እንዲኖራቸው ስለማይፈለግ፥ በዘዴ-በዕርባታ እንዳበቅሉ ይደረጋል። ስለዚህ እንዲህ ዓይነቱ ላም ቀንድ አይኖረውም፤ ምክንያቱም ፈረስ ነውና። ”

፨፨፨፨

• ሚስትህ ወ'ት አለች?

ሙላ ነስሩዲን በጥርስ ህመም ምክንያት ሊሞት እንደሚችል ተነግሮት ነበር። ጓደኛውን፥ ”ለመፈወስ ምን ማድረግ ማድረግ አለብኝ?” ብሎ ይጠይቃል።

“ምን ማድረግ እንዳለብህ ልንገርህ!” አለ፤ ጓደኛው። ”እኔ ጥርሴን አሞኝ በነበረበት ጊዜ፥ ከሚስቴ ጋር ተኝቼ ነበር። እናም፥ ስታቅፈኝ፥ ስትደባብሰኝ ወዲያውኑ ህመሜን ረሳሁት። ”

ነስሩዲን ገጹ ፈካና፥ ”እንዴ! በጣም ጥሩ ነው! አሁን ሚስትህ ቤት ነው ያለችው?” አለ።

፨፨፨፨

• ችሮታ

አንድ የታወቀ ዘራፊና ነፍሰ-ገዳይ ሙላን ያስቆምና፥ ”ርቦኛል! የተወሰነ ገንዘብ እንድትሰጠኝ እፈልጋለሁ።” ይለዋል፥ ”...ደግሞ ምንም ዝባዝንኬ እንዳትለፈልፍብኝ! ”

“ይህንን በምስማቴ ደስታ ተጫጭኖኛል። ምክንያቱም በግልጽ ‹ስጠኝ› ብለህ ጠየቅኸኝ። ‹አበድረኝ› ብትለኝ ኖሮ፥ አጣላህ ነበር። ”

⁘⁘⁘

• ሙያ ቢሱ

ሙላ ነስሩዲን ስለቤተሰቦቹ ለመጠጥ አጣጮቹ እያወጋ ነው፥

“ዘጠኝ ወንድ ልጆች አሉኝ፤ ጥሩዎች ናቸው-ከአብዱል በቀር። እሱ የተማረው ስለማንበብ ብቻ ነው፤ እንደሌሎቹ ስለሙያ አይደለም። ”

⁘⁘⁘

• ተሳስቼ ነው!

ሙላ ነስሩዲን ቤቱ ገባና ከሚስቱ ጋር መጨቃጨቅ ጀመረ።

“እንደገና? !” አጉረመረመ፥ ”በዚህ ሰዓት ምን ያስለፈልፍሻል? ”

“አንተ ነህ የምታስለፈልፈኝ!” ሚስት መለሰች፥ ”ለምን እህቴን ስልክ ደውለህ ሰደብካት? ”

“ጥሩ አቤቱታ ነው። እኔ’ኮ አንቼን ያዋራሁ መስሎኝ ነበር። ለካንስ እሷ ነበረች? ”

፡፡፡፡፡

• አልፎኛል

አውቶብሱ በጣም ተጨናንቋል፤ አንዲት አሮጊት ከጭንቅንቁ መሃል ይታያሉ። ሙላ ሁኔታውን አስተውሎ፥ ለአሮጊቱ ተነሳ። አሮጊቷም “እግዜር ይስጥልኝ!” ብላ፥ ነስሩዲን ተመልሶ እንዲቀመት አደረገችው። ለሁለተኛ ጊዜ ተነሳ፤ እንደገና “ተቀመጥ” አለችው።

በመጨረሻ፥ ሙላ “መነሳት አለብኝ፥ አትዬ! ከምወርድበት ፌርማታ በብዙ እርቄያለሁ! ”

፡፡፡፡፡

• ድንኳኑ

አንድ የዕድር ኮሚቴ አባል ነስሩዲንን አስጠርቶ፥ ”የጠራሁህ ዓመታዊ መዋጮ እንድታዋጣ ነው፤ የሃዘን ድንኳኑን በሌላ ለመቀየር አስበናል።” አለው፥ ”ባለፈው ዓመት የተወሰነ ብር አዋጥተሃል። ”

“ምን? !” ነስሩዲን ገርሞት፥ ”አስ’ካሁን ድንኳኑን አልለወጣችሁትም? ”

፡፡፡፡፡

• የሰማይ መና

ሙላ ነስሩዲን ብዙ ብድር ከሰው ተበድሮ፥ በዕዳ ተይዟል። ግን ምንም አይመስለውም። በእውነቱ፥ የተቻለውን ያህል ከፍሎ ለመጨረስ አስቦ ነበር፤ አልሆነለትም እንጂ። አንድ ቀን-ታዲያ-የምሳ ግብዣ ላይ በተገኘበት ጊዜ፥ ”ዕዳህን መክፈል ሳትችል፥ እንዴት እዚህ ግብዣ ላይ ልታገኝ ቻልክ?” ብሎ፤ አንድ አበዳሪው ይጠይቀዋል።

“ታውቃለህ፤ አሁን የምጠጣውን ሻምፓኝ ገበያ ስለማላገኘው ነው የመጣሁት። ደግሞ ለአንተም ብድር፥ ለሻምፓኙ የምከፍለው ገንዘብ የለኝም።” መለሰ፤ ነስሩዲን።

፡፡፡፡፡

- **ምርጫ**

ሙላ ነስሩዲን ቀንከሌት እየለፋ ነው፤ የሞት ሽረት ትግል ላይ ነው-ለሁለተኛ ጊዜ ለመመረጥ። እናም፥ አንድ ምሽት ላይ ራሱን እያዝናና በነበረበት ወቅት(ከቅስቀሳ ንግግር በኋላ)፥ ጓደኛው ጥያቄ ይሰነዝርበታል፥

“ንግግሮችህን አዳመጥኩ። ግን የከነከነኝ አንድ ነገር አለ። ዳግም ብትመረጥ፥ ምን ለማድረግ አስበሃል? ”

“ዋናው ነጥብ እርሱ አይደለም፤ ጃል። ‹ባልመረጥስ? › የሚለው ነው-ለኔ ዋና ትኩረት።” አለ፤ ነስሩዲን።

⁘⁘⁘

• መሳቅ እንደህመም

አንድ ወጣት ሰባኪ ከስራው ጋር ራሱን በማለማመድ ላይ ይገኛል። ከግዴታዎቹ መካከል በሽተኞች የሞሉበትን ሆስፒታል መጎብኘት አንደኛው ነው። ሆስፒታሉ ውስጥ ነስሩዲን ተኝቶ ነበር፤ በመኪና አደጋ ምክንያት። የሰባኪውም ምዕመን ነው። ሙላ በጣም ተጎድቷል። አንድ እግሩ ተሰብሯል፥ ሁለት እጆቹ ተሰብረዋል፥ አንገቱ’ጋ ያሉት አጥንቶቹ ተሰብረዋል፥ ፊቱ ተገጣጥቧል፥ የራስ ቅሉም ተጎድቷል። የጎድን አጥንቱም ተሰብሯል። ሰውነቱ በሙሉ በፋሻ ተሸብልሎ፥ ሁለቱ ዓይኖቹና ከንፈሮቹ ብቻ ይታያል። ወጣቱ ሰባኪ ይህንን ባዬ ጊዜ ተረብሾ አንደበቱ ተዘጋ። ግን አንድ ነገር መናገር እንዳለበት አመነ። ስለዚህም ሙላን ጠየቀው፥

“ዛሬ ምን ይሰማሃል? የተሰበሩት አጥንቶችና የተላላጡ ቆዳዎች ትልቅ የህመም ምንጭ ሆነውብሃል። አይደለምን? ”

“አይ! ብዙም አያመኝም። ያው ስስቅ ካላመመኝ’ንጂ! ”

:::::

- **መሻሻጥ**

መካኒኩ ለጓደኛው-ለሙላ ነስሩዲን አንድ የተበላሸ መኪና ሰርቶ ይሸጥለታል። በነጋታው ሲያስብ ግን ይጸጽተዋል፤ እንደገና ከሙላ ለመግዛት ይወስናል። ቤቱ ሄደና፥ ”መኪናውን ካንተ መግዛት እፈልጋለሁ፤ የሃምሳ ብር ትርፍ ታገኛለህ።” ነስሩዲን ለመካኒኩ ይሸጥለታል። በኋላ-ሲያስበው-ይቆጨዋል። ስለዚህ ወደመካኒኩ ቤት ይሄዳል።

“ይቅርታ! መኪናዋን መልሰህ እንድትሸጥልኝ እፈልጋለሁ። ያው የሰባ አምስት ብር ትርፍ ታገኛለህ።” ይልና ሙላ ከመካኒኩ ይገዛል። መካኒኩም ይጸጽተውና ከሙላ መኪናውን ይገዛል፤ ሙቶ ብር ለሙላ ጨምሮ። አሁንም መኪናው ሲወስድበት፥ ሙላ አዘነና ወደመካኒኩ አመራ። አጅር መካኒክ ያን መኪና ላ’ንድ ድርጅት ሸጦት ኖሯል።

“አንተ ደደብ! ለምን ለሌላ ሰው ትሰጠዋለህ? ለኔ አትሸጥልኝም ነበር?” አለ፤ ሙላ፥ ”በተለይ፥ እርስበርሳችን ስንሻሻጥ፥ ጥሩ የሆነ ማህበራዊ ግንኙነት ይኖረን ነበር። ”

• ሰይጣኑ ጋር

ሙላ ነስሩዲን በጣም እየጠጣ ጓደኞቹን ይጎነታትል ነበር፤ ጓደኞቹም መጠጣቱን እንዲተው፥ አንድ ዘዴ ቀየሱ።

ሙላ እንደለመደው እየተወለካከፈ ሲሄድ፥ አንዱ ጓደኛው-ልክ እንደሰይጣን ለብሶ፥ ቀንድና ጭራ ተክሎ፤ ከተደበቀበት ጢሻ ዘልሎ ይወጣል።

ከፊቱ ቆሞ፥ ”ከዛሬ ጀምሮ መጠጥ መጠጣት የለብህም!” ይለዋል፤ እንደሰይጣን ድምጹን አጎርንኖ።

“አንተ ማነህ?” ሙላ፤ ጠየቀ።

“እኔ’ማ ሰይጣን ነኝ! ”

“ስለተዋወቅኩህ ደስ ብሎኛል። እኔ የእህትህ ባለቤት ነኝ። ”

⁞⁞⁞⁞

• አያ'ዎ!

ሙላ ነስሩዲን ከዛፍ ስር ተቀምጦ፥ ከጎረቤቱ ጋር ወሬውን ይሰለቅጣል። እያወራ በነበረበት ጊዜ፥ አንድ ህጻን ልጅ ከመንገድ ዶሮ ይዞ ይመጣል።

“ዶሮዋን ከየት አገኘሃት?” ነስሩዲን ህጻኑን ጠየቀ።

“ሰርቄያት ነው።” አለ፤ ህጻኑ።

ሙላ ነስሩዲን ፊቱን ወደጎረቤቱ አዙሮ፥ በኢድናቆት መናገር ጀመረ፥ ”ይህ የኔ ልጅ ነው። ይሰርቃል፤ ግን አይዋሸኝም። ”

⁘⁘⁘

• ስሁቱ ጥያቄ

“ላለፉት ሁለት ሰዓታት ደብዛህን ያጠፋኸው ለምንደነው?” አለች፤ የሰውዬው ሚስት።

“ከሙላ ነስሩዲን ጋር ፖስታ ቤቱ አካባቢ ተገናኝተን ነበር። ግን አንድ ስህተት ፈጸምኩ፤ ‹አሁን ምን ይሰማሃል? › ብዬ ጠየቅኩት።” አለ፤ ሰውዬው።

⁘⁘⁘

• ልዋጭ

ሙላ ነስሩዲንና ጓደኞቹ መንገድ ዳር ከሚገን ሳራማ መስክ ላይ በጀርባቸው ተንጋልለው ያወራሉ። ከሁሉም በላይ አቃጣይዋ ጸሃይ አለች፤ በሰማዩ ላይ ወፎች ወዲያ-ወዲህ ይላሉ። ሁሉም ነገር ረጋ ያለና ሰላማዊ ነው።

“ወገን! ሚሊየን ብር ቢሰጠኝ እንኳ፥ ይህንን አካባቢ ለቅቄ አልሄድም።” ሙላ ነስሩዲን።

“አምስት ሚሊየን ብር ቢሰጥህስ?” አንዱ ጓደኛው ጠየቀ።

“ምን ገንዘብ ቢበዛ፥ ይህንን ቦታ አለቅቅም!” መለሰ ነስሩዲን።

“አንድ ብር ቢሰጥህስ?” ሌላኛው ጠየቀ።

ሙላ ተነሳና፥ ”አሁን ጥሩ አላችሁ፤ በተለይ አንተኛው። አሁን ገና ዕውነተኛውን የብር መጠን ጠራችሁ!” አለ።

፧፧፧፧፧

- **ፀላኤ ጭቅጭቅ**

ሙላ ነስሩዲን፡-”አሽግ ሲጃራ ስጠኝ’ስቲ! ”

ሻጭ፡-”እሺ፥ ጌታዬ። መደበኛውን ወይስ ሌላኛውን? ”

ነስሩዲን፡-”ሌላኛውን...ያ ሁልጊዜ የምወስደውን። ”

ሻጭ፡-”ፊልተር ያለው ወይስ የሌለው? ”

ነስሩዲን፡-”ፊልተር ያለው። ”

ሻጭ፡-”ኒኮቲን ያለው ወይሰ የሌለው? ”

ነስሩዲን፡-”ኒኮቲን ያለው። ”

ሻጭ፡-”በነጠላ ወይስ በእሽግ? ”

ነስሩዲን፡-”በእሽግ። ”

ሻጭ፡-”የቱርክ ወይስ...”

ነስሩዲን፡-”ተወው በቃ! ማጨሱን ትቼዋለሁ! ”

፡፡፡፡፡

• የሚስት ዳፋ

ሙላ ነስሩዲን ወደዶክተሩ ቢሮ ገባ፤ ቁርጭምጭሚቱ ለምሷል።

“በጌታ ስም!” አማታበ፤ ዶክተሩ፥ ”ምን ያህል ጊዜ አሳለፍክ-አንዲህ ከሆንክ? ”

“ሶስት ሳምንት አስቆጥሬያለሁ!” አለ፤ ሙላ።

“አንደዚህ ቁርጭምጭሚትህ እስከሚለምስ ለምን ቆየህ?” ጠየቀ፤ ዶክተሩ።

“ጥሩ፥ በጣም አመንትቼ ነበር። ሁልጊዜ እኔ ላይ መጥፎ ነገር ነው የሚደርስብኝ። ሚስቴ ‹አታጭስ› ብላ ሙጭጭ አለችብኝ፤ ወይኔ! ”

⁜⁜⁜

• ለመርሳት መጣር

ሙላ ነስሩዲን ራት ላይ ሁልጊዜ፥ ፊቱንና እጁን ሳይታጠብ ነበር የሚቀርበው።

“ሂድና ታጠብ!” ሚስቱ አምባረቀችበት፥ ”ሁሌ እነግርሃለሁ። አንተ ግን ያው ነህ-ሳትጣጠብ ትመጣለህ። መቼ ነው-እኔ ሳልጮኽብህ ታጥበህ የምትቀርበው? ”

“ጥሩ፥ ማን ያውቃል? አንድ ቀን አለመታጠቤን ትረሺው ይሆናል ብዬ ነው። ”

⁜⁜⁜

- ***ፀገም***

ሙላ ነስሩዲን ከሚኒስትሩ ጋር ይገናኝና ስለጎረቤቶቹ አሳዛኝ የድህነት ታሪክ እየተናገረ ነው፥

“ይህቺ ድሃ-ባሏ የሞተባት ሴት፥ ከአራት የተራቡ ልጆቿ ጋር ትኖራለች። የምታቀምሳቸው-የምታልሳቸው አጥታለች። ደግሞም ሴትዮዋ ታምማለች። ለመታከም ገንዘብ የላትም። ለቤት ኪራይ 100ብር ማውጣት አለባት፤ ግን የላትም። ኪራዩ ለሶስት ወር ነው የሚከፈለው። ካልከፈለች ትባረራለች። እኔም እሷን ለማገዝ ተፍ-ተፍ እያልኩ ነው። አንተ-በተለይ-መርዳት ከቻልክ...”

“እችላለሁ!” አለ፤ ሚኒስትሩ፥ ”አንተ ለመርዳት ከተነሳህ፥ እኔም እችላለሁ። በነገራችን ላይ አንተ ማነህ? ”

“እኔ ባለርዕስት ነኝ!” አለ፤ ነስሩዲን።

፡፡፡፡፡

• አላዋቂነት

የሙላ ነስሩዲን ሚስት የገበጣ ጨዋታ ህግ ጠንቅቃ ታውቃለች፤ ነስሩዲን ግን እንደወረደ ነው። እናም፥ አንድ ምሽት ላይ የሰፈሩ ሰው ተሰብስቦ ገበጣ ሲጫወት፥ ሙላ ቆሞ ይመለከታል።

"ተመልከች! እኔ ምንም የማላውቅ፥ ስለገበጣ የማላውቅ አድርገሽ ትገምቺያለሽ! አይንሽ ላይ ይነበባል!" አላት፤ ሚስቱን።

"ውይ-ውዴ! በትክክል-ራሱ-ብትጫወት፥ ምንም የምታውቀው ነገር የለም።" አለች፤ ሚስት።

⁘⁘⁘

• ወረፋው

ነጋዴው የደንበኛ ጋጋታ እርቦታል፤ ድንገት አንዲት ባልቴት ዘው ብላ ስትገባ፥ ነጋዴው ይነቃል። ስጋ ነው የሚነግደው።

"ሩብ ኪሎ ለጥብስ የሚሆንና ግማሽ ኪሎ የድመት ስጋ መዝንልኝ! ቸኩያለሁ በጣም!" አለች፤ በከልቢያ። ዘወር ብላ ስታይ፥ ነስሩዲን ከኋላዋ ቆሟል።

"ይቅርታ! እንግዲህ ብዙ ላስጠብቅህ ነው!" ስትለው፤ እርሱም ቀበል አድርጎ፥ "ከራበሽ ችግር የለም። እቆማለሁ!" አላት፤ በተሸሞነሞነ ቅላጼ።

⁘⁘⁘

• ተመሳስሎሽ

ነስሩዲን ከሽፍታው ጋር ተገጣጠመ፤ ሁለቱም ሰከረዋል። በሽፍታው እጅ ላይ ሽጉጥ ይታያል። ”ለመሞት ተዘጋጅ!” ሽፍታው ሙላ ላይ ዛቻ ጣለ። ”አንተ ላይ አሁኑኑ እተኩሳለሁ። ”

“ለምን ትተኩስብኛለህ?” ጠየቀ፤ ነስሩዲን።

“ሁልጊዜ ‹እኔን የሚመስል ሰው ላይ እተኩሳለሁ! › እያልኩ እናገራለሁ፤ ለምዶብኝ ነው። ”

“ታዲያ! እኔ አንተን እመስላለሁ?” ደግሞ ጠየቀ፤ ነስሩዲን።

“ትመስላለህ! ”

“ተኩስብኛ! አንተን በጣሙን እመስላለሁ! ተኩስብኛ! ”

፧፧፧፧

• ንዴት

ባልና ሚስት አንድ የመዝናና ቦታ ላይ እየተዝናኑ ነው። የምኝታ ክፍላቸውን ካጸዳዱ በኋላ፥ የሻወሩን ቧንቧ ረስተው ሳይዘጉት ቀሩ። ከግማሽ ሰዓት ቆይታ፥ ነስሩዲን ካለበት ክፍል መስኮቱ ከፍቶ፥ አንገቱን ወደውጭ አስገገ። ወደ ላይ አንጋጥጦ ሲመለከት፥ ባልዬው ኣይኑን አቆርዝዞ ሲተክዝ አየ።

“አንተ ሰው!” ተጣራ፤ ነስሩዲን።

“ምነው? ችግር አለ?” ጠየቀ፤ ባልዬው።

“ሻወሩን ዝጋው! እየፈሰሰ ነው! ...ከፍት ሆኖ ይረብሸኛል!” አጉረመረመ።

“እሺእዘጋዋለሁ። ትንሽ ደቂቃ ታገሰኝ! ”

ሰውዬው ወደክፍሉ አንገቱን ለመመለስ ተሰናዳ፥ ”ደሞ ኢታጉረምርም! ከኔ ጋር ሚስቴ አለች። ”

“እንዴ! እኔ ምን ይገ፫ ነው-እዚህ የመጣሁት? እንስሳ?” አሁንም ባረቀ፤ ነስሩዲን።

⁘⁘⁘

• ያልተፈወሰ በሽታ

ሙላ የበጋውን ወር በሽርሽር እየገፋው ነው። ከሽርሽሮቹ በአንዱ፥ ከአንድ-ከዚህ በፊት አክሞት ከነበረው ሃኪም ጋር መንገድ ላይ ይገጣጠማሉ። ”ትዝ ይለኛል! ሪህ በሽታ ይዞኝ ወደአንተ መጥቼ ነበር። በደንብ አክመህን-ይኸው-ተፈውሻለሁ። አስታወስከ?” ሙላ ጠየቀው።

“አ...ዎ፥ አዎ...ትዝ ይለኛል!” በእንትብታቤ ዶክተሩ መለሰ።

“ጥሩ! ፥ መቼም ፥ ገላህን ‹ታጠብ› እንደማትለኝ አምናለሁ፤ ምክንያቱም ስታጠብ፥ አንተ ‹አከምኩት› ያልከው በሽታ ይነሳብኛልና። ”

፡፡፡፡፡

• ሴት? ወንድ?

የወላጆች-መምህራን ኮሚቴ ውይይት በጣም ጦፏል። ሴትና ወንድ መምህራን ጎራ ለይተው ይከራከራሉ።

“እኔ ‘ምለው ሴት መምህራን ምርጥ ናቸው።” አለች፤ አንዲት ለፍላፊና አረበ-ሰፊ ሴት። ”ሴት ባትኖር ኖሮ፥ ወንድ ምን ይሆን ነበር? ”

“ገነት ውስጥ ሃብሃብ እየበላ በቀላሉ ይኖር ነበር።” ሙላ ነስሩዲን ከበስተኋላ በኩል ጮኸ።

፡፡፡፡፡

• የመጨረሻ መለኪያ

ሙላ ነስሩዲን መጠጥ ቤት ውስጥ ተወዝፏል፤ ከጎኑ ከተቀመጠውም ሰው ጋር ወግ ጀምሯል።

“አንድ መለኪያ ብቻ ከጠጣሁ፥ በጣም እሰክራለሁ።” አለ፤ ሙላ።

“ከምር?” ጠየቀ፤ እንግዳው ሰው፥ ”አንድ ብቻ? ”

“አዎን! ደግሞ የመጨረሻው መለኪያ በ...ጣም ያጠዘኛል! ”

⁘⁘⁘

• መታከት

የእንግዳ መቀበያ ክፍሉ ወንበሮች በሙሉ ተይዘዋል። ሁሉም ሰው ቆሞ፥ ዶክተሩን ይጠብቃል። ዶክተሩ ምንም ቃል አልተነፈሰም። መጨረሻ ላይ ሙላ ነስሩዲን ተነሳና፥ ”ጥሩ፥ ቤቴ ሄጄ አላህ ነፍሴን ቢወስዳት ይሻላል።” ብሎ፥ ወደበሩ አመራ።

⁘⁘⁘

• ጠንካራው ውሻ

ሙላ ነስሩዲን ውሻ ከጎረቤት ለማሳደግ ይወስዳል፤ ስለውሻው ጥሩ-ጥሩ ነገር ለጓደኛው እያወራ ነው።

“ዝም ብሎ ውሻ እንዳመስልህ! ሌባ ወደደጃችን ድርሽ አይልም-እርሱ ካለ። ምክንያቱም አነፍናፊ አፍንጫ አለውና። ”

“ሌላስ? ሌባ ሲገባ፥ ምን ያደርጋል?” ጠየቀ፤ ጓደኛው። ”...ጮሆ ጎረቤት ይቀሰቅሳል? ”

“አይደለም፤ እንዴ...እንደዚህ’ማ አያደርግም። ከአልጋዬ ስር ሲጫወት ነው-የሚያድረው፥ የሚውለው። ”

⁘⁘⁘⁘

• የሴት ግብር

ሙላ ነስሩዲን መጠጥ ቤት ውስጥ እያለቀሰ ምሬቱን ማዝነብ ጀመረ፥

“እኔ ምንም አልጨነቅም፤ ሁሉንም ነገር የምታስተዳድረው ሚስቴ ናት። ገንዘቤን የምሰጠው ለሚስቴ ነው፤ አማቷ ደግሞ በገንዘብ የራሷን ቤት ትገነባለች። ለካስ! ላቤን እያንጠፈጠፍኩ የማመጣው ገንዘብ፥ ለ’ነርሱ ነው የምገብረው። ”

⁘⁘⁘

• መጠጡ

ጓደኛው በጣም ርካሽ የሆነ አረቄ ይሰጠዋል፤ ሙላ ነስሩዲን ልደቱን በሚያከብርበት ዕለት። ቆይቶ ጓደኛው ሙላን ስጦታው ‹እንዴት ነው? ‹ ብሎ ይጠይቀዋል። ሙላ፥ ”ፎርጅዱን እንኳን አልገዛሽው። ትክክለኛውን ነው የሰጠሽኝ።” አለ።

“ምን ማለትህ ነው?” ጠየቀ፤ ጓደኛው።

“ከዚህ ከፍ ያለ ስጦታ ሰጥተሽኝ አታውቅም። በመጥፎው ጊዜ ደግሞ የዘቀጠ መጠጥ ትሰጠኛለሽ። ስለዚህ ካ’ንተ ጥሩ ነገር አልጠብቅም፤ ከመጠጥ በስተቀር”

⁘⁘⁘

• ታቃጥላለች...

ሙላ ነስሩዲን እና ጓደኛው ስለሚስቶቻቸው እያወሩ ነው።

“የኔ ሚስት በጣም ትናደዳለች።” አለ፤ ጓደኛው፥ ”በትንሽ ነገር ትናደዳለች። ”

“በጣም ዕድለኛ ነህ። የኔዋ ግን እኔን ታቃጥላለች።” አለ፤ ሙላ።

⁞⁞⁞

• ፍንክንክ

ብዙ ጓደኞቹ መጠጥ እንዲያቆም ይመክሩታል፤ ሙላም “እሺ” አላቸው። ”ወደቤት መሄድ አለብኝ።” አለ፤ እየተንቦጀቦጀ። ”ቤት ሄጄ መጠጥ ስለማቆሜ፥ ለሚስቴ መናገር አለብኝ። ”

“ለምን ትነግራታለህ?” አንዱ ጓደኛው ጠየቀ።

“አላውቅም። ለነገሩ ቤቴ አልሄድም! ”

⁞⁞⁞

- **ሁለቱን ለምን?**

“ይህ መጽሃፍ የምትሰራውን ስራ በግማሹ ያቃልልሃል።” አለ፤ አንድ መጽሃፍ ሻጭ።

ይህን የሰማው ሙላ ነስሩዲን እንዲህ አለ፥ ”ጥሩ፥ ሁለቱንም እገዛሃለሁ።”

⁘⁘⁘

- **ፍሬ ከናፍር**

ሙላ ነስሩዲን ሁልግዜ እንዲህ ይል ነበር፥

“ሚስትህ በትኩረት እንድትሰማህ ከፈለግህ፥ የምታወራውን ወሬ ለሌላኛዋ ሴት አንሾካሹከህ አውራላት። ”

⁘⁘⁘

• ማብሸቅ በሙዚቃ

ሙላ ነስሩዲን የጺየሞ ተጫዋቹን በጣም ለመነው።

“ጥሩ፥ ምን አይነት ሙዚቃ ልጫወትልህ?” ጠየቀው፥ ”ምን ልጫወት? ”

“የፈለግከውን...”አለ፤ ነስሩዲን፥ ”ግን ጎረቤቶቼን የሚያናድድ ሙዚቃ መሆን አለበት። ”

⁜⁜⁜

• ንብረቶቼን

ሙላ ነስሩዲን በወንበዴዎች በጩቤ ተወጋ። ለመሞት በቀሩት ትንሽ ደቂቃ ውስጥ ለሚስቱ ደብዳቤ ሊጽፍላት አሰበ፤ ከሆስፒታል። ወደደብዳቤው መገባደጃ አካባቢ የጻፈው አረፍተ-ነገር እንደሚከተለው ይነበባል፥

“ከመወጋቴ አንድ ቀን በፊት አስቀድሞ፥ አስፈላጊ ንብረቶቼን-ገንዘቤን-የባንክ ደብተሬን እዛው ባንክ ቤት አስቀምጬያለሁ። እናም፥ በጣም የሚቆጨኝ ይህቺን ዓለም በሞት መሰናበቴ አይደለም፤ ንብረቶቼን ጥዬ መሞቴ እንጂ! ”

⁜⁜⁜

• ልጅነትን መፈለግ

አንድ ጋዚጠኛ በሙላ ነስሩዲን 105ኛ ዓመት የልደት በዓል ላይ ተገኝ፤ ሙላን ለማናገር። እንዳጋጣሚ ነስሩዲን ህጻናት የሚለብሱትን ልብስ በትልቁ አሰፍቶ ለብሷል።

“ይቅርታ አድርግልኝና የትንንሾችን ልብስ በመልበስ፥ ልጅነት አገኛለሁ ብለኽ ታምናለህ?” ብሎ ጠየቀው።

“አዎ፤ ሚስቴ ስትነግረኝ፥ ‹ልጅነትህን ላለማራቅ ህጻን መስለህ መኖር አለብህ› ትለኛለች። የምፈልገውን ነገር ከፈለግኩ መሆን ነው ያለብኝ። ”

፡፡፡፡፡

• ብዝኀ-ስህተት

ሙላ ነስሩዲን 100ኛ ዓመት የልደት በዓሉን አስመልክቶ ከአንድ ጋዜጠኛ ጋር ቃለመጠይቅ እያደረገ ነው።

“እንደገና ተወልደህ ‹ኑር› ብትባል፥ እስከአሁን የሰራሃቸውን ስህተቶች ዳግም ትፈጽማቸዋለህ?” ሲል፤ ጠየቀው።

“እንዴታ!” መለሰ፤ ሽማግሌው ነስሩዲን፥ ”እንዲያውም ከበፊቱ የባሱ-ዕጥፍ ስህተቶችን ነው የምሰራው። ”

፡፡፡፡፡

• ትመጣለህ! ትመጣለህ!

አንድ ጎብኚ ወደእነመላ ነስሩዲን መንደር ዘለቀ። ቀኑ ተገጣጠመና እሱ በገባበት ጊዜ፥ የሙላ ነስሩዲን 99ኛ ዓመት ልደት በዓል እየተከበረ ነበር። ከነዋሪዎቹ ጋር ሲበላ-ሲጠጣ ከቆየ በኋላ፥ ለመሄድ ተነሳ። ቱሪስቱ ሙላን ጨበጠና፥ ”የሚቀጥለው ዓመት ልደትህን ለማክበር ወደዚህ እንደምመጣ ተስፋ አደርጋለሁ።” ይለዋል።

“ለምን ለመምጣት እንደማይቻልህ እንጃ! በጣም ጤነኛ ነህ! ስለዚህ ትመጣለህ!” አለ፤ ”ሼባው” ነስሩዲን።

⁘⁘⁘

• «ማረጀት ፀረ-ሞት ነው!»

ሙላ ነስሩዲን 95ኛ ዓመት የልደት በዓሉን እያከበረ ነው፤ በዚህን ጊዜ አንድ የቅርብ ጓደኛው አንዲህ ሲል ይጠይቀዋል፥

“ማርጀት ያስጠላል አይደል? ”

“እንዴ! አያስጠላም! እኔ እንዲህ ባላረጅ ኖሮ፥ እሞት ነበር።” ሲል፤ መለሰለት።

⁘⁘⁘

• ህመም

“የግራ እግርህ ህመም ከእርጅና ጋር የተያያዘ ነው።” ብሎ ለሙላ ነስሩዲን ይነግረዋል፤ ሃኪሙ።

“ይህ ሊሆን አይችልም።” መለሰ፤ ሙላ፥ ”ይህ ህመም በዕድሜ ብዛት ከመጣ፥ ለምን የቀኝ እግሬን አያመኝም? ”

፨፨፨

• «ሰብዓዊ መብት ይከበር!»

የሙላ ነስሩዲን ሚስት ባሏን ከዕንቅልፉ አዚሙ እየነጣጠለችው ነው፥

“ፍቅሬ፥ ተነሳ! ዛሬ እኮ 42ኛ ዓመት የጋብቻ በዓላችን ነው። በደመቀ ሁኔታ እናከብረዋለን። ዶሮዋን ብታርድልኝ ምን ይመስልሃል? ”

ሙላ አተኩሮ እያያት መለሰ፥

“ይህቺን ምስኪን ዶሮ የዛሬ 42 ዓመት ለተፈጸመ ጋብቻ ለምን እንሰዋታለን? ዶሮዬቱ ከምትታረድ፥ በዓሉ ባይከበር ይሻላል። ”

፨፨፨

• በአባቱ የወጣ ልጅ

አንድ አስተማሪ ለአብዱል እናት ደብዳቤ ይጽፍላታል፥

“ይድረስ ለእመት(የነስሩዲን ሚስት)! ልጅዎ አብዱል በጣም ጎበዝ ተማሪ ነው። ግን ሴት አውል ነው። ይህንን ባህርይውን ለማስተውና ከሴቶች እርሱን ለመነጠል እየሞከርኩ ነው። ”

“ሙከራህ እንዲሳካ ምኞቴ ነው። ባህርይውን ለማሻሻል ምን ዓይነት ሙከራ እንዳደረግክ ብትነግረኝ፥ እኔም አግዝህ ነበር። አባትዬውም እንደአብዱል ሴት አውል ነው፤ የአባቱን ጠባይ ለማረም ቀን ተሌት እየለፋሁ ነው። እባክህ! የልጄን አንተ ተወጣልኝ! ”

⁞⁞⁞⁞⁞

• የተዝናኖት ጉዞ

“ወደገነት መግባት የምትፈልጉ ወገኖች፥ ተነሱ!” ወጣቱ ሰባኪ ጮኸ። ይሄኔ ሁሉም ተነሳ፤ ከሙላ በስተቀር። ሰባኪው ተገርሞ፥ ”ወንድም! ወደገነት መግባት አትፈልግም?” ብሎ ይጠይቀዋል።

“አልፈልግም፥ ወዳጄ። እየተዝናናሁ እምሄድ ካልሆነ፥ ለምን እነሳለሁ?” ጥያቄውን በጥያቄ መለሰ።

⁘⁘⁘

• ምኞት

“የኔ ሚስት ፒያኖ ትጫወት ነበር።” አለ፤ የሙላ ጓደኛ፥ ”ልጆቼ ከተወለዱ በኋላ፥ መጫወት አቆመች እንጂ! ”

“አንዳንዴ ልጆች ምኞትን ይፈጥራሉ፤ አይደለምን?” ሙላ ነስሩዲን።

⁘⁘⁘

• ምክሩ

አንዲት ወጣት ሴት ምክር ፈልጋ ወደሙላ ነስሩዲን ቤት ሄደች። ሙላን፥ ”ሁልጊዜ የሚዋሸኝን ልጅ ባገባ ይሻላል? ወይስ አይሻልም?” ብላ ጠየቀችው።

“ይሻላል፤ ለዘላለሙ ማግባት ካልፈለግሽ!” አላት፤ ነስሩዲን።

፨፨፨

• ተፈላጊው በቅሎ

የሙላ ነስሩዲን ሚስት በበቅሎ ጭንቅላቷ ላይ ተመትታ ትሞታለች። ለቀብሩ ስነ-ስርዓት በርካታ ሰው ይወጣል። አንድ ሚኒስትር የሰውን ጋጋታ እያዩ፥ ”ይህቺ ሴትዮ በጣም ታዋቂ መሆን አለባት፤ ይህን ያህል ህዝብ ስራወን ትቶ፥ ለቀብሯ የወጣው ሴትዮዋ ታዋቂ ብትሆን ነው።” ብለው ለሙላ ነስሩዲን ይነግሩታል።

“ይሄ ሁሉ ሰው የወጣው ለቀብር አይደለም። እሷን የመታውን በቅሎ ለመጫረት ብሎ ነው የወጣው።” ሲል መለሰለት፤ ሙላ።

፨፨፨

• ተነቃዩ ጥርስ

የሙላ ነስሩዲን ሚስት ሞታለች፤ በዚህ ወቅት አንድ ሰው ወደቤት ዘው ብሎ ይገባል። ሙላ የአስክሬን ሳጥኑ’ጋ ጥጉን ይዞ ቆሟል።

“አሄሄ! ...ይህቺ ሴትዮ ምንም ውበት የሚባል ነገር አልፈተረባትም።” አለ፤ ሰውዬው።

“ለምን? ዓመቱን ሙሉ ሆስፒታል ስትመላለስ ከርማለች፤ ለዛ ይሆናል።” መለሰ፤ ነስሩዲን።

፡፡፡፡፡

• ስሞታ

ሽማግሌው ሙላ ነስሩዲን ስለቤቱ ሙቀት-አልባነት ለሴት አከራዩ እተናገረ ነው፥

“አንዳንዴ ወደ ማታ አካባቢ በጣም ይበርደኛል። ኮመዲኖው ላ ያስቀመጥኩት ጥርሴ ሲንቀጫቀጭ ይሰማኛል። ”

፡፡፡፡፡

• ውርስ

የሙላ ነስሩዲን ሚስት ሆስፒታል ውስጥ ለመሞት እያጣጣረች ነው፤ ከመሞቷ በፊት ከጎኗ ወንበር ይዞ ለተቀመጠው ባሏ የሆነ ነገር እያወራችው ነው፥

“ውዴ! ስሞት የሚቆጨኝ አንድ ነገር አለ። አንተን ብቸኛ አድርጌ መሄዴ፥ ሁሌም ቢሆን ይጸጽተኛል። ሌላ ሴት ማግባት ከፈለግክ አሁኑኑ ንገረኝ፤ በኔ ፈቃድ ስር መሄድ ከሻትክ። ግን አንድ ነገር ቃል ግባልኝ? ”

“ምን ቃል ልግባልሽ?” ጠየቀ፤ ነስሩዲን።

“አዲስ ሚስት የምታገባ ከሆነ፥ የኔን አሮጌ ልብሶች እንዳትለብስ አድርጋት። ቃል ግባልኝ! ”

“ቃል እገባልሻለሁ። ግን ሁሉም ልብሶችሽ ለፋጢማ ልክ አይደሉም፤ ልብሶችሽን ልትለብሳቸው አትችልም።” አላት፤ ነስሩዲን።

⁘⁘⁘

- **ኬረዳሽ**

አንድ ሰካራም ከሙላ ጋር አውቶብስ ውስጥ ተቀምጧል። ሰካራሙ ሙላ ነስሩዲን የሃይማኖት አባት እንደሆነ ጠርጥሯል። ጥርጣሬውን ለማረጋገጥ፥ ”እኔ ወደገነት አልገባም፤ ገነት የሚባልም ነገር የለም!” ብሎ ፎከረ።

ነስሩዲን ዝም አለ።

“ገነት የሚባል የለም! ”

አሁንም ዝም አለ።

“እኔ ወደገነት አልገባም! ”

ሙላ ዘወር አለና፥ ”ገነት ከሌለ፥ ለምን ወደገሃነም አትገባም? ›ለማንኛውም፥ ዝም በል! አታደንቁረኝ!” ብሎ ገሠጸው።

፧፧፧፧፧

- **ዕውነታ**

የሙላ ነስሩዲን ሚስት ስለጋብቻ ህይወት ለልጇ ትነግራታለች፤ አንዳንድ ለየት ያሉ ዕውነታዎችን ጨምራ።

“በእናንተ ጊዜ ህይወት ቀላል የሚሆን ይመስለኛል፤ ከእኛ ዘመን የእናንተ ይሻላል። ለ55 ዓመት ተጋብተን በምንኖርበት ወቅት፥ ሁለት ነገሮችን ማስተዳደር ተስኖኝ ነበር። የመጀመሪያው አባትሽ፥ ሁለተኛ የምድጃ እሳት። ሁለቱንም-ሁልጊዜ መቆጣጠር አለብኝ። ግን አንደኛው ሹልክ ብሎ ይጠፋል። ”

፨፨፨፨

• ችጋርን መቃረም

ሙላ ነስሩዲን የጓደናውን የወደፊት ህይወት መዳፉን በማንበብ እየተነበየ ነው።

“ደሃና ሃዘንተኛ፥ እንዲሁም ጥፋተኛ ሆንህ እስከ 60 ዓመትህ ድረስ ትኖራለህ።” ይለዋል።

“ከዛ በኋላስ?” ተጠንቋዩ በተስፋ ጠየቀ።

“ከዛ በኋላ ከችጋሮችህ ትርፍ ማጋበስ ትጀምራለህ! ”

⁞⁞⁞⁞

• ሃሳዊ ዜና

የሙላ ነስሩዲን ሚስት ቁርስ ለመብላት ገበታው ላይ ተሰየመች። አጠገቧ ያለውን ጋዜጣ አንስታ ለዓይኗ አመል የፊት ገጹን አነበበች። ወደመጨረሻው ጠርዝ አካባቢ፥ የእርሷ ህልፈተ-ህይወት ተጽፏል። ደነገጠችና ለባሏ ስልክ ደወለች። ነስሩዲን ለሌላ ጉዳይ ከከተማ ወጥቷል።

“ጠዋት ላይ የወጣውን ጋዜጣ ተመለከተው፥ ሙላ? እኔ እንደሞትኩ ተደርጎ ተዘግቧል።” አለች፤ ሚስት።

“አንብቤዋለሁ። በነገራችን ላይ፥ አሁን ከየት ሆነሽ ነው የምትደውዪልኝ?” ጠየቀ፤ ነስሩዲን።

⁞⁞⁞⁞

• አማች

ሙላ ነስሩዲን ላሚቷን እያለበ ነው። አንድ ኮርማ እየተንደረደረ ወደሙላ ነስሩዲን ይመጣል። ሙላ ግን ወዴትም አልተንቀሳቀሰም፤ እዛው ቁጭ ብሎ እያለበ ነው። ብዙ ሰው እሱ ወደአለበት አቅጣጫ ይመለከታል፤ ኮርማው እየተንደረደረ ሲመጣ፥ የሙላ ነስሩዲን ያለመሸሽ ነገር በጣም አስገርሞታል። ነስሩዲን አልቦ እንደጨረሰ ተነስቶ ይሄዳል። አንድ ሰው ቀረብ አለና፥ ”የዕውነት አልፈራህም፥ ሙላ?” ሲል ጠየቀው።

“እንዴ! አልፈራሁም፤ ምክንያቱም ቅድም ሳልባት የነበረችው ላም፥ የኮርማው አማች ናትና። ”

꧁꧁꧁꧁

• ተከታይ ተፈንካች

ሰባኪው ሙላ ነስሩዲንን ለመጠየቅ ወደሆስፒታል ሄደ። ነስሩዲን በድብድብ ምክንያት በጣም ተጎድቶ ነበር።

“አሁን ልጸልይልህ ነው። ስለዚህ በድንጋይ የፈነከተህን ሰው ‹ይቅር› ማለት አለብህ።” ይለዋል፤ ሰባኪው።

“ቢሆን ጥሩ ነበር። እዚህ ቁጭ ብለህ፥ እኔ እስከምወጣ ጠብቅ። ከዚያ ሌላ ተፈንካች ሰው ሲመጣ፥ ለእርሱ ጸልይለት።” አለ፤ ሙላ።

⁘⁘⁘⁘

• ጢምቢራን ማጣት

ሰካራሙ ሙላ ነስሩዲን ከፖሊሱ ጋር መንገድ ላይ ይገናኛሉ።

“የት ነው ያለሁት?” ብሎ ይጠይቃል።

“ንዳና ላይ ነው ያለኸው።” ይላል፤ ፖሊሱ።

“ማብራሪያውን ተወውና የት ከተማ እንዳለሁ ንገረኛ? ”

፨፨፨፨

• ዕድል

“ሁሉም ነገር ለበጎ ነው እሚሆነው።” አለ፤ ሚኒስትሩ። ቢሮ ውስጥ ከሙላ ነስሩዲን ጋር እያወሩ ነው። ሚኒስተሩ አሳዛኝ ታሪክ ለሙላ ይተርኩለታል።

“ያ ሰው! ይታይሃል? ! ሚስቱን በመኪና አደጋ አጥቷል!” ሚኒስትሩ ጣታቸውን ወደመስኮቱ አቅጣጫ እየጠነቆሉ።

“ግን ሁሉም ሰው የእርሱን ዓይነት ጥሩ ዕድል አላገኘም፣ ጌታዬ!” አለ፤ ነስሩዲን።

፨፨፨፨

- **መረፃ ደቂአንስቲዮ**

አንድ አዲስ-ገቢ የዩንቨርሲቲ ተማሪ ከሙላ ጋር ስለሴቶች እያወራ ነበር።

“ምን ትመክረኛለህ? አስተዋይ ሴት ወይስ ቆንጆ ሴት ላግባ?” ብሎ ይጠይቀዋል።

“ሁለቱንም ማግባት የምትችል አይመስለኝም።” መለሰ፤ ነስሩዲን።

“እንዴት? ”

“መልሱ ግልጽ ነው። ቆንጆዋ ሴት ሁለመናዋ ጥሩ ነው፤ ከአንተ የበለጠች ናት። አስተዋይዋ ደግሞ ከአንተ የበለጠ ታውቃለች። ”

⁘⁘⁘⁘

• ሰርቆ መመለስ

ሙላ ነስሩዲን በመስረቁ ምክንያት ይከሰሳል። ፍርድ ቤት ቀርቦ ይከራከራል። ዳኛውም ጠጠር ያለ ማስረጃ ሰላላገኙ፥ አንዲለቀቅ ወሰናሉ። ሙላ ግን ነገሩን በቅጡ አልተረዳም።

“ጉዳይህ በዚህ አብቅቷል፤ በነጻ ተለቅቀሃል። መሄድ ትችላለህ! ”

“ጥሩ፥ አመሰግናለሁ-ክቡር ዳኛ። ግን አሳማውን መልሴ ለባለቤቱ መስጠት አለብኝ?” ጠየቀ፤ ሙላ።

⁘⁘⁘

• ስሜትን መግፋት

ሙላ ነስሩዲን አንድ ወጣት ገጣሚ የሰጠውን የግጥም ነዶ አንብቦ ጨረሰ፤ እንደጨረሰም ለባለቤቱ መለሰ።

“ብዙ የስሜት እሳት ወደግጥሞቹ ብጨምር ምን ይመስልሃል?” ወጣቱ ነስሩዲንን ጠየቀ።

“አይሻልም፤ እንዲያውም ተቃራኒውን ብትፈጽም ጥሩ የሚሆንልህ ይመስለኛል።

⁘⁘⁘

• ክህደትን ፍለጋ

ሙላ ነስሩዲን በሚስቱ ሁለመናው ይፈተሽ ነበር። ከልብሱ ቅንጣት የሴት ጠጉር ለማግኘት ብላ ነበር የምትፈትሸው፤ የክህደት ሰበብ ፈልጋ። ታዲያ፥ አንድ ምሽት ልብሱን በትኩረት ፈትሻ፥ ምንም የሴት ጠጉር ሳታገኝ ትቀራለች።

“አሁን ደግሞ ከራሰ-በራ ሴት ጋር መውጣት ጀመርክ። ”ብላ አምባረቀችበት።

⁘⁘⁘

• ብድርን መግፋት

ሰወዬው ከሙላ ነስሩዲን ጋር ለመገናኘት ወደቤት ይሄዳል። በጣም ይዋደዱ ነበር-ከጓደኛው ጋር። ግን ለ6 ዓመታት ተያይተው አያውቁም፤ ተገናኝተውም አያውቁም። ጓደኛው ስለአሳለፈው ችጋር፥ ስለሚስቱና ልጆቹ መሞትና ስለውስጡ ህመም ለሙላ በሰፊው ያወራል። አውርቶ ሲጨርስ፥ ሙላን ብድር ይጠይቃል። ሙላም ልጁን ጠራና እንዲህ አለው፥

“ልጄ! ይህንን የማይረባ ወደዛ ጣልልኝ! ልቤን በጣሙን ሰብሮታል! ”

⁘⁘⁘

- **ጨረታው**

...በመጨረሻ፥ ነስሩዲን በቀቀኑን በጨረታ ይገዛል፤ ከብዙ ገንዘብ በኋላ። ሙላ አጫራቹን፥ ”የሚያወራ ወፍ ይመስለኛል።” ይለዋል፤ በቀቀኑን እየተመለከተ።

“ያወራል?” ጠየቀ፤ አጫራቹ።

“ማን መሰለህ ላለፉት አራት ሰዓታት አንተ ላይ ሲጫረት የነበረው? በቀቀኑ አልነበረምን?” ጥያቄውን በጥያቄ እየመለሰ።

፡፡፡፡፡

• ማስጠሎ ፅሁፍ

አርታዒው የሙላ ነስሩዲንን ጽሁፍ ለማንበብ እየታገለ ነው።

“ሙላ! የእጅ ጽሁፍህ በጣም ያስጠላል፤ ለማንበብ አይመችም።” አለ፤ አርታዒው፥ ”መጀመሪያ ግጥሞችህን ለምን አስተይበህ አትመጣም ነበር? ”

“አስተይብ? መተየቡንስ ልተይብ! ግጥለመጻፍ ካባከንኩት ጊዜ በላይ ላባክን ነው። ምን ዓይነት ትዕዛዝ ነው? !” እያለቃቀሰ ጠየቀ።

፨፨፨፨፨

• ዕውነተኛ አመንዝራ

የሙላ ነስሩዲን ልጅ የፖለቲካል ሳይንስ ተማሪ ነው። አንድ ቀን አባቱን እንዲህ ሲል ይጠይቀዋል፥

“አባባ! በፖለቲካ ውስጥ ከሃዲ ሰው ምን ዓይነት ነው? ”

“ፓርቲያቸንን ጥሎ የሚወጣ ሰው ሁሉ ከሃዲ ነው።” መለሰ፤ ነስሩዲን፥ ”እናም፥ ወደሌላ ፓርቲ ገብቶ ነገር የሚፈተፍት ከሃዲ ነው። ”

“ጥሩ! ከአንዱ ፓርቲ ወደአናንተ የሚመጣ ሰው ምንድነው የሚባለው?” ደግሞ ጠየቀ።

“እርሱማ አመንዝራ ነው፥ ልጄ! ዕውነተኛው አመንዝራ! ”

⁘⁘⁘⁘

• ችጋርን መሻት

ሙላ ነስሩዲን የተወሰነ ብር በሰጠው ሃብታም እጅጉን ቀና። ሰውዬውም መቅናቱን አውቆ፥ ”በኔ ላይ ለመቅናት ምንም ምክንያት የለህም። የደላኝ መስሎ ቢታይህም፥ እኔ ብዙ ችግሮች ያሉብኝ ሰው ነኝ!” አለው።

“የተወሰኑ ችግሮችን አጋብሰህ ይሆናል። ልዩነታችን ግን አዚህ’ጋ ነው፤ እኔ እንደአንተ ብዙ ችግር አያጋጥመኝም!” አለ፤ ነስሩዲን።

⁜⁜⁜

• ችግርን መጠበቅ

አንድ የጋዜጣ አዘጋጅ በጣሙን ተናድዷል። ከሙላ ነስሩዲን ጋር ሻይ ቤት ውስጥ ይገናኛሉ። ”ለዛሬ በምን ዙሪያ አተኩረን ዜና እንስራ-ለፊት ገጽ የሚሆን? በከተማይቱ ውስጥ ምንም ችግር አልተፈጠረም፤ ባለፉት 24 ሰዓታት።” ሙላን ይጠይቃል።

“ችግር የለም። አንድ ችግር ይፈጠር ይሆናል። አንተ ግን ቶሎ ተስፋ አትቁረጥ! ጽና!” ብሎ መለሰለት።

፡፡፡፡፡

• ግብግቡ

“ግብግቡ በጣ አሰልቺ ነው!” አንድ እንግዳ ለሙላ ነስሩዲን ይናገራል፤ የራት ግብግ ላይ። ”ይህቺን መለኪያ ልጨርስ እንጂ አዚህ’ማ አልቆይም! ”

“እኔም፤ ግን ትንሽ መቆየት አለብኝ። አዘጋጁ እኔ ነኝ!” አለ፤ ነስሩዲን።

፡፡፡፡፡

• ኮንሰርቱ

አንድ እንግዳ ከነስሩዲን ጎን ይቀመጣል፤ የሙዚቃ ድግሱ እየተሳለጠ ነው። እንደተቀመጠ፥ ድምጹን ዝቅ አድርጎ ዘፋኟ ላይ ትችት ያወርድ ገባ፥

“በጣም የሚያስጠላ ድምጽ ነው ያላት። ታውቃታለህ ግን? ”

“አዎ፤ አውቃታለሁ። ሚስቴ ናት! ”

ሰውዬው ደነገጠና “በጣም ይቅርታ! የምትጫወተው ሙዚቃ በጣም ምርጥ ነው። ግጥሙን የጻፈው ሰው ሊደነቅ ይገባል።” አለ።

“እኔም አደንቀዋለሁ!” ነስሩዲን ተናገረ።

፡፡፡፡፡

- **ተምሳሌተ-ጉንዳን**

“በደንብ ዕረፍት ማድረግ አለብህ!” በስራ ብዛት የዛለ ጓደኛውን እየመከረ ነው።

“ግን በጣም በስራ ተወጣጥሬያለሁ!” ተናገረ፤ ጓደኛው።

“ጉንዳኖችን ተመልከት! ተግተው ይሰራሉ። ግን የዕረፍት ጊዜያቸውን ኤረሱም፤ ይዝናናሉ። አንተም አንደጉንዳኖች ሁን! ”